*Ethiop.j.lang.cult.commun. 2025, 10*(2): 288-316
*Open Access Licensed under Creative Commons: CC BY-NC-ND 4.0*
*Faculty of Humanities-Bahir Dar University*
*ISSN: 2518-2919*
DOI 10.20372/ejlcc.v10i2.1980

**Original Research** **Open Access**

# The nature and causes of kinship formation systems among the Awi community

Emebet Andualem Wasihun
*PhD Candidate, Bahir Dar University, Ethiopia*
Aschalew Abeje (PhD)
*Associate Professor, Bahir Dar University, Ethiopia*
Abiyu Asmamaw (PhD)
*Assistant Professor, Bahir Dar University, Ethiopia*

*Corresponding author:* Emebetandualem50@gmail.com

## Abstract

This study aimed to investigate the meaning of kinship and causes of kinship formation among the Awi society from emic perspectives. The study employed an ethnographic research method and triangulated data, which were collected through in-depth interviews and focus group discussions. The data were analyzed using thematic analysis method. The findings revealed that kinship among the Awi society has both biological and social components. The study showed that kinship in this society is a way of helping, solving economic problems, strengthening social relations, restoring psychological damage, and maintaining traditional order. Therefore, in this society, it has been shown that social kinship has a significant contribution to the survival of the community, no less than blood kinship. The study also identified that among the Awi society, reasons for the formation of kinship include creating a conducive trade and trade environment, combating feelings of isolation, loneliness, and poverty. Therefore, we argue that the issues that lead to the creation of kinship involve fulfillments of people's needs, interests, and desires in both a physical and spiritual sense.

Keywords: Awi, kinship, nature of kinship, kinship systems, reasons for creating kinship.

**Citation:** Emebet Andualem, Aschalew Abeje & Abiyu Asmamaw. (2025). The nature and causes of kinship formation systems among the Awi community. *EJLCC, 10*(2).288-316. DOI 10.20372/ejlcc.v10i2.1980

*Submitted: April 2025* | *Revised: October 2025* | *Accepted: November 2025*

**©2025 Author(s). All rights reserved**

*Ethiop.j.lang.cult.commun. 2025, 10*(2): 288-316 *Faculty of Humanities-Bahir Dar University*
*Open Access Licensed under Creative Commons:* *ISSN: 2518-2919*
*CC BY-NC-ND 4.0*
DOI 10.20372/ejlcc.v10i2.1980

# የዝምድና ምንነት እና መፍጠሪያ ምክንያቶች በአዊ ማህበረሰብ

## አፅህሮተ ፅሁፍ

ይህ ጥናት በአዊ ማህበረሰብ ዘንድ የዝምድና ምንነትን እና የዝምድና መፍጠሪያ ምክንያቶችን መመርመር ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ በጥናቱ የተነሱ ርዕሰ ጉዳዮች ከማህበረሰቡ እውቀትና አመለካከት አንፃር የተመረመሩ ሲሆን ጥናቱ አይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ነው፡፡ በጥናቱ የተነሱ ጥያቄዎች ዝምድና ምን ማለት ነው? እንዴትስ ይገለፃል? ዝምድና እንዲፈጠር የሚገፉ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው? የሚሉት ሲሆኑ የተነሱ ጥያቄዎችን ለመመለስ ያስቻሉ የተመሳከሩ መረጃዎች በጥልቅ ቃለ መጠይቅ እና በቡድን ተኮር ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰሰቡ ሲሆን የተገኙት መረጃዎች የጭብጥ ትንተና (thematic analaysis) ዘዴን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡ በጥናቱ ግኝት መሰረት በአዊ ማህበረሰብ ዘንድ ዝምድና ስነ ህይወታዊ እና ማህበራዊ ይዘት ያለው ሲሆን ፍቅር እና ሰላም መስበኪያነት፣ መረዳጃና መጠቃቀሚያነት፣ ችግር መፍቻ እና ማህበራዊ ግንኙነትን ማጠንከሪያነት፣ ምጣኔ ሃብታዊ ችግርን መፍቻነት፣ ስነ ልቡናዊ ጉዳትን መጠገኛነት እና ባህላዊ ስርዓትን ማስቀጠያነት ሆኖ የሚያገለግል ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡ ማህበራዊ ዝምድና በዚህ ማህበረሰብ ዘንድ የሰዎችን ምጣኔ ሃብታዊ፣ ማህበራዊ እና ስነ ልቡናዊ ጉዳዮችን በመፍታት በኩል ከስጋ ዝምድና ባልተናነሰ ለማህበረሰቡ ህልውና ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያበረክት እንደሆነ ጥናቱ ጠቁሟል፡፡ በተጨማሪም በጥናቱ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው በአዊ ማህበረሰብ ዘንድ ዝምድና እንዲፈጠር ምክንያት (ሰበብ) የሆኑ ጉዳዮች ምቹ ንግድ እና የንግድ ከባቢን ለመፍጠር፣ ከእንግዳነት ስሜት ለመውጣት፣ ከብቸኝነት ለማምለጥ እና ከድህነት ለመዳን የሚሉት እንደሆኑ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ በመሆኑም ዝምድና እንዲፈጠር ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች የሰዎችን ፍላጎት፣ ጥቅም፣ ምኞት በጥቅሉ ስጋዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶች እንዲሟሉ የሚያደርግ ይዘት እንዳላቸው ጥናቱ አመላክቷል፡፡

**ቁልፍ ቃላት**:- አዊ፣ ዝምድና፣ የዝምድና ምንነት፣ የዝምድና ስርዓት፣ የዝምድና መፍጠሪያ ምክንያቶች

# መግቢያ

Mhaiske et al. (2016) [1] “የሰው ልጅ በተፈጥሮው ማህበራዊ ነው፤ ከተለያዩ ሰዎች ጋር በተለያየ መንገድ ግንኙነቶችን ወይም መስተጋብሮችን መስርቶ የሚኖር ማህበራዊ እንስሳ ነው” ይላል (P. 1):: ስለሆነም የሰው ልጅ በተናጠል ከመኖር ይልቅ አብሮነትን፣ ቡድናዊነትን እና መረዳዳትን የሚመርጥ ነው። ስለሆነም በረጅም የህይወት ተመክሮው ግለሰቦችን ወደ ቡድናዊነት ለማምጣት የተለያዩ የማዛመጃ ስርዓቶችን ዘርግቷል። ማህበረሰቡ የማዛመጃ ስርዓቶችን ሲፈጥር ደግሞ እንዲሁ ዝም ብሎ ሳይሆን ከኋላ የሚገፉ የተለያዩ ጉዳዮች አስገድደውት ነው። አንዱ የጥናቱ ትኩረትም ዝምድና ከማህበረሰቡ አመለካከት እና እይታ አንፃር እንዴት ተበይኗል (ተተርጉሟል) ከሚለው ባሻገር የአዊ ማህበረሰብ በተለያዩ የዝምድና መፍጠሪያ ስርዓቶች እንዲዛመድ ምክንያት (ሰበብ) የሆኑት ጉዳዮች ምንድን ናቸው? የሚሉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። ስለሆነም ምንነት ከማህበረሰብ እይታ አንፃር እና እንዲፈጠር ምክንያት (ሰበብ) የሆኑ ጉዳዮች ከማህበረሰቡ የረጅም የኑሮ ልምድ (ተመክሮ) አንፃር መተንተን የጥናቱ ዋና ትኩረቶች ናቸው።

## የጥናቱ ዳራ

Schneider (2004) “ዝምድና አለማቀፋዊ ይዘት ያለው የሰው ልጆችን ግንኙነት የሚያረጋግጥና በህይወት ውስጥ አስፈላጊው ማህበራዊ ትስስር መፍጠሪያ መዋቅር ነው”ይላል (p.14)። Mhaiske et al. (2016) በተመሳሳይ ደግሞ “ዝምድና በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ያለ በዘር ወይም በደም እንዲሁም በጋብቻ ምክንያት የሚፈጠር የሰው ልጆችን ግንኙነት እውቅና መስጫ፣ ማረጋገጫ እና ማፅኛ መንገድ ነው” ይላል (p.23)። የዝምድና ፅንሰ ሃሳብ በብዙ አቅጣጫ የሚታይ ሰፊ ርዕሰ ጉዳይ ነው። ይህን በተመለከተም Read (2018) ዝምድና አለማቀፋዊ እና ርዕሰ ጉዳዩ ከተለያዩ ትልልቅ ጉዳዮች አንፃር የሚታይ መሆኑን ጠቁሞ ከሃይማኖታዊ፣ ከኢኮኖሚያዊ፣ ከፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ስርዓቶች ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው እንደሆነ አስረድቷል (p. 1)።

ዝምድና ባለፈባቸው የጥናት ታሪኮችም ብዙ ያከራከረ፣ ሰፊ በተለያዩ አቅጣጫ የሚታይ እንደሆነ እና በስነ ሰብዕ የጥናት መስክ

---

[1] በእንግሊዝኛ የተፃፉ ስራዎች የህትመት ዘመናቸው እንደ ጎርጎሮሳውያን አቆጣጠር ሲሆን በአማርኛ የሰፈሩ ስራዎች ደግሞ አቆጣጠራቸው በአመተ ምህረት ነው።

መጠናት ከጀመረ ረጅም ጊዜ ማስቆጠሩን (Abebayehu & Dejene, 2019; Sahlins, 2013) ገልፀዋል፡፡ የአፈጣጠር ስርዓቱን በተመለከተም እስካሁን ባለው የጥናት ታሪክ ሶስት አይነት ሃሳቦች ሲራመዱ ቆይተዋል፡፡ የመጀመሪያው Sousa (2003) and Brown (1950) እንደሚሉት ዝምድና ስነ ህይወታዊ (biological) ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ማለት ዝምድና ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ በዘር (በመወለድ) የሚገኝ ነው ማለት ነው፡፡ Sousa (2003) ይህን ሃሳብ ሲያረጋግጥም እንዲህ ይላል፡- "ዝምድና ማለት በስነ ህይወታዊ ግንኙነት ግልፅ የሆነ የዘር ሃረግ ያለውን ተዋረዳዊ አመጣጥ የሚመለከት ሲሆን ለዝምድና ዋና መስፈርቱ ተመሳሳይ መሆን ወይም በዘር ግንድ መሰረት በተዋረድ መምጣት ነው" ብሏል፡፡

በተጨማሪም Brown (1950) "ሁለት ሰዎች ዘመድ ናቸው ካልን በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ዝምድና አላቸው፤ ወይም አንዱ ከሌላው የተወለደ ነው፣ ወይም ሁለቱም ከአንድ የዘር ግንድ የተወለዱ ናቸው፣ ስለዚህ ዝምድና በዘር ላይ የተመሰረተ ሲሆን በመጀመሪያ የዝምድና አይነቱን የሚወስነው የዘር ግንድ የሚታወቅበት እና የሚቆጠርበት መንገድ ነው" ይላል (p. 1)፡፡ በዚህኛው ሃሳብ መሰረት ዝምድና መወለድ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ ሁለተኛው ሃሳብ ደግሞ (Durkheim, 1898; Gennep, 1906; Sahlins, 2013) እንደሚሉት "Kinship is social not Biology"(306) የሚል ነው፡፡ ይህን ሃሳብ በሚያራምዱ ተመራማሪዎች መሰረት የሚቀነቀነው ዋናው ጉዳይ የዝምድና ማህበራዊነት ነው፡፡

ስለሆነም የዚህ ሃሳብ አቀንቃኞች ዝምድናን የማህበረሰቡ የአኗኗር ሁኔታ፣ የኑሮ ልምዱ እና ባህሉ የሚሰራው፣ የሚፈጥረው እንጂ ስነ ህይወታዊ ወይም ተፈጥሮአዊ አይደለም የሚሉ ናቸው፡፡ Durkheim (1898) ይህን ሃሳብ አፅንኦት ሲሰጥ all kinship is social or cultural ብሏል፡፡ Gennep (1906) በተመሳሳይም ዝምድና ማህበራዊ ስርዓት መሆኑን እንደሚከተለው ያብራራል፡ "kinship is not simply a matter of birth or the facts of biology. Free of biological referents."(p.43). እነዚህ ምሁራን ዝምድና ዝም ብሎ የመወለድ ጉዳይ እንዳልሆነ እና ከማህበራዊነት እና ከባህላዊነት ጋር የሚገናኝ ፅንሰ ሃሳብ መሆኑን የሚያስረዱ ናቸው፡፡

ከእነዚህ በተጨማሪ ደግሞ ዝምድና የዘር ቆጠራ ጉዳይ አለመሆኑን Marks (2002) "kinship is not a genetic property" (p.251) በሚል ገልጧል፡፡ በዚህ ሃሳብ መሰረት ዝምድና የዘር ቆጠራ ጉዳይን ዋና ርዕሰ ጉዳይ የሚያደርግ አይደለም፡፡ ስለሆነም ከተፈጥሯዊነቱ ይልቅ በማህበራዊነቱ እና በባህላዊነቱ ላይ የሚያተኩር

ነው፡፡ በሶስተኛ ደረጃ የመጣው ሃሳብ ደግሞ kinship is both social and biological የሚል ነው፡፡ ይህን ሃሳብ ከሚያራምዱ ምሁራን ውስጥ (James, 2008; Gellner, 1958; Crossman, 2019; Schneider, 2004) የሚጠቀሱ ሲሆን ዝምድናን ለመበየን መወለድ ብቻውንም ሆነ ባህላዊነት ወይም ማህበራዊነት ብቻውን በቂ አይደለም የሚሉ ናቸው፡፡ James (2008) በዚህ ጉዳይ ላይ በምሳሌዎች አስደግፎ ሲገልፅ ዝምድና የደም ግንኙነትን፣ የጋብቻ ግንኙነትን እና የጉዲፈቻን ፅንሰ ሃሳብ አጠቃሎ ይይዛል በሚል የዝምድናን ተፈጥሯዊነት እና ባህል የሚፈጥረው መሆኑን አስረድቷል (p. 4)፡፡ ስለሆነም በእነዚህ ሃሳብ አራማጆች መሰረት ዝምድናን ይህ ነው ብሎ ለማለት ማህበራዊነቱም ስነ ህይወታዊነቱም አስፈላጊ ናቸው የሚሉ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ክርክሮች ወጣ ሲል ደግሞ ምሁራን በፅንሰ ሃሳብ ብያኔው ላይ ምን ይላሉ የሚለውን በአጭሩ እንመልከት፡፡

Schneider (2004) የዝምድናን ምንነት እንዲህ በማለት ይገልፃል፡-"The degree of sharing likelihood among individuals from different communities. For instance, if two people have many similarities between them then both of them do have a bond of kinship."(p.240). ሃሳብ የሚገልፀው ሰዎች ከተለያዩ ማህበረሰቦች የወጡ ሊሆኑ ይችላሉ ነገር ግን የሚጋሩት ነገር ካላቸው ለምሳሌ ሁለት ሰዎች ብዙ የሚያመሳስላቸው ነገር ካላቸው በመካከላቸው ዝምድና እንዳላቸው የሚያስረዳ ነው፡፡ Gellner (1958)ም ይህን ሃሳብ የሚጋራ ነው፡፡ ከዚህ ሃሳብ ጋር ተቀራራቢነት ያለው ሌላው ሃሳብ ደግሞ የSahlins (2013) ሃሳብ ሲሆን ዝምድና ማለት “mutuality of being”(p.2) ነው ይላል፡፡ በsahlins ሃሳብ መሰረት ዝምድና ማለት በመኖር ውስጥ መጋራት ነው የሚል ብያኔ ያለው መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡ Sahlins (2013) ሰዎች የሚጋሩት ወይም የሚያገናኛቸው ነገር መሬት፣ የደም ግንኙነት ወይም ቅድመ አያት ነው ብሏል፡፡ በእነዚህ በሁለቱ ምሁራን ሃሳብ መሰረት ዝምድና ማለት በአንድ ጉዳይ ላይ መጋራት ነው፡፡ የሚጋሩት ነገር ከደም፣ ከመሬት እና ከቅድመ አያት በተጨማሪ ችግር፣ ደስታ እና የተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮችን ነው፡፡ Kuper (2018) ደግሞ “kinship is a symbolic discourse. It discourses about ‘mutuality of being’ or ‘common substance” (p. 4) ይለዋል ፡፡ Kuper ደግሞ የsahlinsን ሃሳብ እና የ Schneider ን ሃሳብ ጠቅለል አድርጎ ገልጧል፡፡ ስለሆነም በምሁራኑ ሃሳብ መሰረት ዝምድና “በመኖር ውስጥ መጋራት” ወይም “ሰዎችን ሊያገናኝ የሚችል የጋራ ነገር መኖር” በሚሉ ፅንሰ ሃሳቦች ተበይኗል፡፡

የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት Read (2018) እንደሚለው ዝምድና እጅግ ሰፊ ፅንሰ ሃሳብ ነው፡፡ ከጉዳዩ ትልቅነት እና ሰፊነት አንፃር ግን በእኛ ሃገር ደረጃ ብዙ ያልተጠና ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን ምንም አይነት ሙከራዎች አልተደረጉም ማለት አይደለም፡፡ አጥኚዋ እስካሁን ባደረገችው ዳሰሳ በዝምድና ዙሪያ የተጠኑ ጥናቶች በሚከተሉት ይዘቶች ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው በዝምድና ስርዓት ውስጥ ስለሚገኙ ስያሜዎች (Getie, 1998; Hashim et al., 2016)፣ ሁለተኛ ደግሞ በዝምድና ስርዓት ውስጥ ስለሚካሄደው የዘመድ ግንኙነት ከበራ ክዋኔውን መተንተን ላይ (እመቤት, 2012) እና ደመቀ (2012)፤ ሌላው በስጋ ዝምድና ስለሚገኙ ዘመዶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን በተመለከተ ተችሎት (2012) ሲሆን ሌሎች ደግሞ የዝምድና መፍጠሪያ ስርዓቶችን ክዋኔ ማብራራት ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው (አለምነው፣ 2005፤ አፈወርቅ፣ 2009፤ ሰሚራ፣ 2006፤ ሽመልስ፣ 2008፤ ዝናሽ፣ 2004፤ ገነት፣ 2013፤ አጃኢባት፣ 2011፤ ስንታየሁ፣ 2008፤ አያሌው፣ 2011፤ መሃመድ፣ 2012፤ ብሩክ፣ 2013)፡፡ ከላይ አጥኚዎች ያነሷቸው ነጥቦች በአንድም በሌላም መንገድ በዝምድና ላይ የሚያጠነጥኑ ናቸው፡፡ ሆኖም ግን በእነሱ እና በዚህ ጥናት መካከል የሚከተሉት ልዩነቶች ተስተውለዋል፡፡

የመጀመሪያው የርዕስና ትንተና አለመገናኜት ነው (ርዕሱን ዝምድና አድርገው በውስጡ ስለሌላ ርዕሰ ጉዳይ መተንተን)፡፡ ይህም አንዳንዶቹ ጥናቶች ዝምድናን እንደርዕሰ ጉዳይ አንስተው በትንታኔ ክፍላቸው ምሳሌያዊ ንግግር ላይ እና የዘመድ ግንኙነት ከበራን ማብራራት ላይ ማተኮራቸው ነው፡፡ ዝምድና ርዕሰ ጉዳይ ሆኖ ከቀረበ ዝምድናን በተገቢው መንገድ መግለፅ ይገባ ነበር ብየ አምናለሁ፡፡ በዚህ ጥናት የትንተና ክፍል ግን የተነሳውን ርዕሰ ጉዳይ የተመለከቱ ሃሳቦች እና ትርጓሜዎች የተተነተኑበት ነው፡፡

ሁለተኛው ደግሞ ዝምድናን ካጠኑበት ማህበረሰብ እይታ (perspective) አንፃር ምን ይለዋል ወይም እንዴት ይገልፀዋል የሚለውን እና ምክንያቱን የትኛውም ጥናት አልተመለከተም፡፡ የዚህ ጥናት ግን አንዱ እና ዋነኛው ዓላማው ዝምድና ከማህበረሰቡ እይታ፣ አመለካከት እና እውቀት አንፃር እንዴት እንደተገለፀ መፈተሽ ስለነበር የማህበረሰቡን እውቀት ከትርጓሜ እና ከምክንያት አንፃር አንፀባርቋል፡፡ ሶስተኛው ከስነ ዘዴ አንፃር ነው፡፡ ክለሳ ያደረግኳቸው አብዛኞቹ ጥናቶች ክዋኔዎች ላይ ያተኮሩ ስለሆኑ ምልከታን እንደዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተጠቀሙ ናቸው፡፡ ይህ ጥናት ግን የማህበረሰቡን የተጠራቀመ እውቀት፣ ፍልስፍና፣ አመለካከት እና እምነት መፈተሽ ላይ ትኩረት ያደረገ ስለሆነ ጥልቅ ቃለመጠይቅ እና ቡድን ተኮር ውይይትን

በመጠቀም የተሰራ ነው። ስለሆነም ጥናቱ ለክዋኔ ብዙ ትኩረት አልሰጠም።

አራተኛው ደግሞ ከማህበረሰብ ምርጫ ወይም ከቦታ አንፃር ነው፡ ፡ ከላይ የተጠቀሱ ጥናቶች የተለያዩ ክልሎችን እና አካባቢዎችን ጠቅሰው የተጠኑ ናቸው። ነገር ግን በአዊ ማህበረሰብ የዝምድና ስርዓት ዙሪያ የተጠና ምንም አይነት ጥናት አልተገኘም። ስለሆነም የአዊ ማህበረሰብን ዝምድና ምንነቱን እና እንዲፈጠር ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች ከማህበረሰቡ የረጅም የኑሮ ልምድ አንፃር ቢጠና በዘርፉ የጥናት መስክ አዲስ እውቀት ይጨምራል ከሚል ሃሳብ የተሰራ ነው።

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአዊ ማህበረሰብ ዘንድ የዝምድናን ምንነት እና እንዲፈጠር ምክንያት የሆኑ ጉዳዮችን ማብራራት ነው። ከዚህ ዋና አላማ በመነሳት ጥናቱ ሁለት ንዑስ አላማዎች አሉት። የመጀመሪያው የአዊ ማህበረሰብ ዝምድናን ከረጅም የኑሮ ልምዱ እና እውቀቱ አንፃር እንዴት ብሎ ይገልፀዋል? እንዴት ይተረጉመዋል የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በማህበረሰቡ ዘንድ ዝምድና እንዲፈጠር የሚገፉፉ ምክንያቶች ምን እንደሆኑ መለየት የሚሉት ናቸው። በዚህ መሰረትም የዚህ ጥናት ጥያቄዎች ዝምድና ምን ማለት ነው? እንዴትስ ይገለፃል? ዝምድና እንዲፈጠር የሚገፉ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው? የሚሉት ናቸው።

ጥናቱ ከተለያዩ ውስንነቶች አንፃር በርዕሰ ጉዳይ እና በቦታ የተወሰነ ነው። ከላይ እንደተጠቀመው ከርዕሰ ጉዳይ አንፃር በዝምድና ስርዓት ውስጥ የዝምድና ምንነቱ እና እንዲፈጠር ምክንያት ከሆኑ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ነው። ከማህበረሰብ አንፃር ደግሞ የአዊ ዞንን ማህበረሰብ የሚመለከት ሆኖ መነሻ ያደረግኩት በዞኑ ካሉ ወረዳዎች ውስጥ በጓንጓ ወረዳ የሚገኘውን የአዊ ማህበረሰብ ነው። በዚህ ወረዳ የሚገኘውን ማህበረሰብ የመረጥኩበት ምክንያት ከፍተኛ ቁጥር ያለው የአገው ህዝብ የሚኖርበት ቦታ ስለሆነ ነው። የጓንጓ ወረዳ ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት (2006) የወረዳውን አጠቃላይ ገፅታ ሲገልፅ "ነባር አገው" የሚባለው እና ከፍተኛ ቁጥር ያለው የአገው ማህበረሰብ የሚኖረው በዚህ ወረዳ ነው ይላል። ይህን በመቶኛ ሲገልፀው በዚህ ወረዳ 85% የሚሆነው ህዝብ አገው እንደሆነ ነው። በመሆኑም ዝምድናን በተመለከተ ትክክለኛውን የአገው ማንነት ይገልፃል ብዬ ስላሰብኩ ይህን ቦታ መርጬ ሰርቻለሁ።

## ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፍ

ዝምድና በጥናት ታሪኩ በተለያዩ ንድፈ ሃሳቦች ሲጠና ቆይቷል፡፡ የተጠናበትን ንድፈ ሃሳብ በተመለከተ Jones (2011) የዝምድና ስርዓት በሚል በፃፈው ፅሁፉ በገለፀው መሰረት ዝምድና ባለፈባቸው የጥናት ታሪኮች በሚከተሉት ንድፈ ሃሳቦች ተጠንቷል፡፡ በ "Evolution" ንድፈ ሃሳብ፣ በስነ ልቦናዊ ንድፈ ሃሳብ፣ በንፅፅር አተያይ፣ በመዋቅራዊ ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ፣ በመዋቅራዊ ንድፈ ሃሳብ እና በእንስታዊ ንድፈ ሃሳብ ተጠንቷል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ሁለት ንድፈ ሃሳቦች በዝምድና የጥናት ታሪክ ውስጥ ብቅ ብለዋል፡፡ እነዚህም የዝምድና ንድፈ ሃሳብ (kinship theory) እና የዝምድና ማካካሻ ንድፈ ሃሳብ (Compensatory kinship theory"[2] ናቸው፡፡ እነዚህ ንድፈ ሃሳቦች ደግሞ ይህ ጥናት የተጠቀመባቸው ንድፈ ሃሳቦች ሲሆኑ ማብራሪያቸው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የዝምድና ንድፈ ሃሳብ:- ይህን ንድፈ ሃሳብ በማቀንቀን የሚታወቀው የመጀመሪያው ሰው Lewis Henery Morgan(1871) ነው፡፡ የንድፈ ሃሳቡ ዋና የማተኮሪያ ነጥብ የግለሰቦች ግንኙነት የማህበረሰቡን መዋቅር የሚገነባበትን መንገድ የሚመለከት ነው፡፡ ይህ ማለት ሰዎች በደም ግንኙነት፣ በጋብቻ ወይም በጉዲፍቻ ተዛምደው ማህበረሰብን የሚመሰርቱበትን መንገድ የሚመለከት ነው፡፡ ግለሰቦች በጋብቻ ተዛምደው ዝምድናው በሁለቱ ተጋቢዎች ወይም ባልና ሚስቶች ብቻ የሚቆም አይደለም፡፡ ቤተሰብ ይመሰርታሉ ከዚያም ወደ ማህበረሰብ እያደገ እየሰፋ ይሄዳል፡፡ ንድፈ ሃሳቡ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ ይህ ጥናትም ዋና ትኩረቱ ዝምድና ላይ ወይም ግለሰቦች ተገናኝተው ማህበራዊ መዋቅርን የገነቡበትን መንገድ ስለሆነ ንድፈ ሃሳቡ የጥናቱ ዋና የማያ መንገድ ነው፡፡ የማህበረሰቡ መዋቅር በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነ ልቡናዊ እና ባህላዊ ጉዳዮች ይገለፃል፡፡

የዝምድና ማካካሻ ንድፈ ሃሳብ (compensatory kinship theory):- ይህ ንድፈ ሃሳብ በ1984 በ Cardoso የተቀነቀነ ንድፈ ሃሳብ ሲሆን የንድፈ ሃሳቡ ዋና የማተኮሪያ ነጥብ ሰዎች በተፈጥሮአዊም ይሁን በሰው ሰራሽ ምክንያት የስጋ ዝምድናን ሲያጡ ሌሎች የማካካሻ ዝምድናዎች እንደ ጉዲፈቻ እና ሌሎች ከስጋ ዝምድና ውጪ ያሉ የዝምድና መፍጠሪያ ስርዓቶችን ማግኜት አለባቸው የሚል ነው፡፡ ንድፈ ሃሳቡ ዋናው ትኩረቱ ሰዎች በስጋ ዝምድና ማግኜት የሚገባቸውን

[2] Compensatory kinship theory የሚለውን የእንግሊዝኛ ሃረግ የዝምድና ማካካሻ ንድፈ ሃሳብ በሚል የአማርኛ አቻ ትርጉም በመተካት የተጠቀምኩበት ሲሆን Alliance theory የሚለውን ደግሞ ጥምረታዊ ንድፈ ሃሳብ በሚለው አቻ የአማርኛ ትርጉም በመተካት ተጠቅሜበታለሁ፡፡

ዝምድና ሲያጡ የሚጎሉባቸው ብዙ ነገሮች አሉ፤ ስለሆነም እነዚህ ጎዶሎዎችን የሚሞሉ (የሚተኩ) ሌሎች ባህል የሚፈጥራቸው የማካካሻ ዝምድናዎች መኖር አለባቸው የሚል ነው፡፡ ይህ ጥናትም ከስጋ ዝምድና በተጨማሪ ባህል በሚፈጥራቸው ማህበራዊ የዝምድና ስርዓቶች ላይ ትኩረት ተደርጎ የተሰራ ስለሆነ ንድፈ ሃሳቡ ለመተንተኛነት አገልግሏል፡፡

## የጥናቱ ስነ ዘዴ

የዚህ ምርምር ቅርፅ ተንታኝ ስልት (Interpretivism Design) ነው፡፡ ይህ የጥናት ቅርፅ ትኩረት የሚያደርገው በአንድ ማህበረሰብ እምነት፣ አመለካከት እና ፍልስፍና ላይ ሲሆን በዚህ የጥናት ቅርፅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት ናቸው፡፡ ሌላው በዚህ የጥናት ቅርፅ የሚነሳው አንድ እውነት የለም፣ እውነት እንደአውዱ ይወሰናል የሚል ነው፡፡ ይህ ጥናትም ጥልቅ ቃለ መጠይቅን እና ቡድን ተኮር ውይይትን ተጠቅሞ ዝምድናን ከአዊ ማህበረሰብ እምነት፣ አመለካከት እና ፍልስፍና አንፃር የተነተነ ነው፡፡ ጥናቱ አይነታዊ የምርምር ዘዴ ነው፡፡ Creswell እና Creswell (2018) እንሚያብራሩት በአይነታዊ ምርምር ዘዴ የሚጠኑ ጥናቶች የጥናቱን ትክክለኛ ቦታ ወይም አንድ አጥኚ መረጃ በሚሰበስብበት ጊዜ መረጃ ሰጪዎች ከሚኖሩበት ቦታ በመሄድ መሆን እንዳለበት እና መረጃን መሰብሰብ ያለበት ራሱ ቦታው ተገኝቶ እንጂ በሌላ ሰው ወይም በሶስተኛ ወገን መሆን እንደሌለበት የአይነታዊ ምርምር ዘዴን ባህሪያት ሲገልፁ ካስቀመጧቸው ነጥቦች ውስጥ ይጠቀሳሉ፡፡

ስለሆነም ይህ ጥናት የፎክሎር ጥናት እንደመሆኑ የማህበረሰቡን አባላት በቀጥታ አግኝቶ እውቀቱን፣ ፍልስፍናውን፣ አመለካከቱን እና እምነቱን ለመፈተሽ በትክክለኛ መቼት በመገኘት መረጃዎችን በራሴ በአጥኝዋ በመሰብሰብ የተተነተኑ ናቸው፡፡ በአይነታዊ የምርምር ዘዴ ውስጥ ደግሞ ጥናቱ የተከተለው “Approach” ኢትኖግራፊያዊ ነው፡፡ መረጃ አቀባዮችን የመረጥኩባቸው የናሙና ዘዴዎች ሁለት ናቸው፡፡ እነዚህም አላማ ተኮር ናሙና (purposive sumpling) እና ጠቋሚ (መጠቁም) ናሙና (snow ball sampling) ናቸው፡፡

Omid et al. (2024) እንደሚለው አላማ ተኮር የናሙና ዘዴ ለአንድ ጥናት አስፈላጊ ናቸው ተብለው የታመነባቸውን ሰዎች መምረጥ የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡ ስለሆነም አላማ ተኮር ናሙናን የተጠቀምኩበት ምክንያት ለጥናቱ አስፈላጊና ጠቃሚ መረጃ ይሰጣሉ ብዬ ያመንኩባቸውን ሰዎች መምረጥ ስላስቻለኝ ነው፡፡ Mumtaz et al. (2025) ጠቋሚ ናሙና “መጀመሪያ የምንጠይቃቸው ሰዎች ከእነሱ

በበለጠ የጥናቱን መስፈርት በሚያሟላ መልኩ መረጃ ይሰጣሉ ተብለው የታመነባቸውን ሰዎች መጠቆም የሚያስችል ዘዴ ነው” ይላል፡፡ በመሆኑም ጠቋሚ (መጠቁም) (snow ball sampling) የተጠቀምኩት ደግሞ መረጃ ሰጪዎቼ ባነሳሁት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ከእኛ የበለጠ እውቀት አላቸው ብለው ያመኑባቸውን ወይም ባለጉዳይ ናቸው ያሏቸውን ሰዎች እንዲጠቁሙኝ በማስቻሉ ነው፡፡

መረጃ ከቀዳማይ እና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰበ ሲሆን መስክ ከመውጣቴ በፊት ርዕሰ ጉዳዩን በተመለከተ ፅንሰ ሃሳባዊ እና ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት ተካሂዷል፡፡ ከቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ውስጥ ደግሞ ጥልቅ ቃለ መጠይቅ እና ቡድን ተኮር ውይይት (focus group discussion) ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ መረጃው በማስታወሻ ደብተር፣ በድምፅ፣ በቪዲዮ እና በፎቶግራፍ ተሰብስቧል፡፡ ዝምድናን በተመለከተ ማህበረሰቡ ያለውን እውቀት፣ አመለካከት፣ ፍልስፍና፣ እና እምነት ለማውጣት ከሙያ፣ ከፆታ፣ ከማህበራዊ ደረጃ እና ከእድሜ አንፃር የተሰባጠሩ መረጃ ሰጪዎች በጥልቅ ቃለ መጠይቅ ተሳትፈዋል፡፡ ዝምድና ላይ የማህበረሰቡ የጋራ እውቀት ምን እንደሆነ ለማወቅና ማመሳከር የሚያስፈልጋቸውን መረጃዎች ለማረጋገጥ ሁለት የቡድን ተኮር ውይይት ተካሂዷል፡፡ በመጀመሪያው ዙር ስድስት አባላት ያሉት ሲሆን ወንዶች ብቻ የተሳተፉበት ነበር፡፡ ሁለተኛው ዙር የቡድን ተኮር ውይይት ደግሞ ሰባት አባላት የተሳተፉበት ሲሆን ሴቶች እና ወንዶች በጋራ ሃሳብ የሰጡበት ነበር፡፡ መረጃዎቹ የጭብጥ ትንተና (Thematic analaysis) ዘዴን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡ የጭብጥ ትንተናን በተመለከተ Clarke and Braun (2015) የሚከተለውን ሃሳብ ገልጸዋል፡- “Thematic analysis (TA) is a method for identifying, analysing and interpreting patterns of meaning (themes’) within qualitative data”(p.222). የተሰበሰቡ መረጃዎች በጭብጥ በጭብጥ ተከፋፍለው ከያዙት መልዕክት አንፃር የተተረጎሙ እና የተተነተኑ ናቸው፡፡

በመጀመሪያ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተቀዱ እና የተቀረፁ መረጃዎች ወደ ፅሁፍ ተቀይረዋል፡፡ ከመረጃዎች ውስጥ ተመሳሳይ ሃሳብ ያላቸውን ኮድ እየሰጠሁ አስቀምጫለሁ፤ ቀጥሎ ደግሞ መረጃዎችን ደረጃ አስይዣለሁ፡፡ መረጃዎችን ደረጃ ሳስይዝ የትኞቹ ተደጋግመው የተነሱ ናቸው የትኞቹስ ደግሞ አልፎ አልፎ ወይም በስሱ የተነሱ ናቸው የሚለውን መስፈርት በማድረግ ነበር፡፡ መረጃዎቹ ደረጃ ከወጣላቸው በኋላ ከያዙት መልዕክት አንፃር ካቀረብኳቸው ተዛማጅ ፅሁፎች ጋር እያዛመድኩ ተንትኛለሁ፡፡ ቀጥሎ መረጃዎቹ ኮድ

ተሰጥቷቸው ተደራጅተዋል፡፡ ኮድ ከተሰጣቸው በኋላ በምድብ በምድብ ተደራጅተው ከያዙት ጭብጥ ወይም መልዕክት አንፃር ተተንትነዋል፡፡

# የመረጃ ትንተና

## የዝምድና ምንነት በአዊ ማህበረሰብ

የአዊ ማህበረሰብ እንደማንኛውም የማህበረሰብ ክፍል ዝምድና መስርቶ፣ ተጋብቶ እና ተዋልዶ የሚኖር ማህበረሰብ ነው፡፡ ዝምድና በዚህ ማህበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጠው ስርዓት ነው፡፡ ዝምድናን በተመለከተ የጠየቅኳቸው የማህበረሰቡ አባላት ከራሳቸው አመለካከትና እውቀት አንፃር ሃሳብ ሰጥተዋል፡፡ በመሆኑም ዝምድና በአዊ ማህበረሰብ ዘንድ ምን አይነት ትርጓሜ አለው? እንዴትስ ገልፀውታል? የሚለው ጉዳይ በሚከተሉት ጭብጦች ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው፡፡

ፍቅርና ሰላም መስበኪያነት፡- ፍቅር እና ሰላም ዝምድና የሚገለፅባቸው ዋና መሰረቶች ሲሆኑ ለአንድ ማህበረሰብ በሰላም መኖር ትልቅ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡ ሁለት ሰዎች ዝምድና እንዲፈጥሩ በመካከላቸው ፍቅርና ሰላም መኖር አለበት፤ በመካከላቸው ፀብ እና ጥላቻ ያለባቸው ሰዎች ዝምድና አይፈጥሩም በተቻላቸው አቅም ሁሉ ለመራራቅ እና ላለመገናኘት ነው የሚጥሩት፡፡ የኔአለም በሪሁን (ቃ.መ፣ 27/02/2016ዓ.ም) እና አስረሳች አስፋው በቃለ መጠይቅ (08/10/2016) በተከታታይ ዝምድናን ሲገልፁ እንዲህ ይላሉ፡- "ድንግር ፍክር ያኽ" [3](ዝምድና ፍቅር ነው)፡፡ እና "ድንግር ፍክርስስታ እንካንኚስ ፌቴርስታውያኽ" (ዝምድና በፍቅርና በመዋደድ የሚፈጠር ነው) ይላሉ፡፡ ፍቅር ጥቅል ቃል ነው፤ በፍቅር ውስጥ መዋደድ፣ መተሳሰብ፣ መቀራረብ፣ መረዳዳት እና መጠያየቅ ጎልተው የሚታዩ እሴቶች ናቸው፡ ፡ ስለሆነም "ድንግር (ዝምድና) ፍክር ያኽ" ሲል ዝምድና መዋደድን፣ መተሳሰብን፣ መረዳዳትን እና መጠያየቅን የሚገልፅ ትርጓሜ ይኖረዋል፡፡ አስረሳች በፍቅርና በመዋደድ የሚፈጠር መሆኑን ስትገልፅ ዝምድና የሰዎችን ሰላማዊ ግንኙነት፣ ፍቅር፣ መዋደድ የሚገልፅ ይሆናል፡፡ ስለሆነም በሰዎች ዘንድ ጥሩ ግንኙነት እንዲኖር እና ያለውን ፍቅርና ሰላም ማፅኛ እና ማረጋገጫ፣ መዋደዳቸው መፈቃቀራቸው እንዲቀጥል ማድረጊያ መንገድ ዝምድና መፍጠር ነው፡፡ ዝምድና በባህሪው መያዣ ወይም ማሰሪያ ይፈልጋል፤ ሰዎች ሲዋደዱ፣ ሲፋቀሩ በመካከላቸው መለያየት እንዳይኖር በዝምድና ያፀኑታል፡፡ Mhaiske et al. (2016)ም

[3] መረጃ ሰጪዎቼ በአዊኛ ቋንቋ የተናገሯቸውን ሃሳቦች በቀጥታ ወስጄ ከጎኑ በቅንፍ አቻ የአማርኛ ትርጉሙን በማስቀመጥ ተጠቅሜበታለሁ፡፡

ዝምድና የሰዎችን ሰላማዊ ግንኙነት እና ፍቅር ማፅኛ እና ማረጋገጫ መንገድ ዝምድና ነው ይላልና የተነሳው ሃሳብ በዚሁ ምንጭ የተደገፈ ነው፡፡ ሆኖም በዚህኛው ርዕሰ ጉዳይ መሰረት ዝምድና መገለጫው ፍቅር፣ ሰላም፣ መተሳሰሰብ እና ጥሩ ግንኙነት በሚሉ ጉዳዮች ላይ የሚያርፍ ነው፡፡

መረዳጃና መጠቃቀሚያነት፡- በሌላ በኩል ደግሞ ዝምድና በአዊ ማህበረሰብ ዘንድ በመረዳዳት እና በመጠቃቀም ላይ ትኩረት ያደረገ ፅንሰ ሃሳብ ነው፡፡ አቶ ወርቃየሁ (ቃ.መ 22/09/2015ዓ.ም) "ዝምድና መጠቃቀሚያ ነው" ይላል፡፡ በ21/09/2015ዓ.ም ባደረግኩት የቡድን ተኮር ውይይትም የዝምድና እርስ በርስ መጠቃቀሚያነት በስፋት ተነስቷል፡፡ መጠቃቀም የሁለቱን ዝምድና መስራቾች የጋራ ጥቅም የሚመለከት ነው፡፡ ጥቅሙ በአንዱ በኩል ብቻ የሚቀር አይደለም፡፡ ለምሳሌ ጡት መጣባት የዝምድና ስርዓት ሲፈፀም የጡት አባት በሃብቱ የጡት ልጅ በጉልበቱ እንዲረዳዱ እና እንዲጠቃቀሙ በማሰብ የሚፈጠር ነው፡፡ ክርስትና ሲናሳም ደግሞ ክርስትና አንሺው በነፍሱ በኩል ሰማያዊ ፅድቅን በመፈለግ በስጋው በኩል ደግሞ በስራ ጊዜ ለመተጋገዝ፣ በበዓላት ጊዜ ተጠራርቶ ለመብላት እና ለመጠጣት እንዲሁም ለጨዋታ ነው፡፡ የአደራ ልጅ ተቀብሎ ማሳደግ የዝምድና ስርዓትም እንደዚሁ በማህበረሰቡ ዘንድ ልጆች ወላጆቻቸውን በተፈጥሯዊም ሆነ በሰው ሰራሽ ምክንያት ወላጆቻቸውን ወይም አሳዳጊዎቻቸውን ሲያጡ በምትኩ በምጣኔ ሃብቱ ለተሻለ ሰው ሰጥቶ የሚጎልባቸውን ነገር እንዲያገኙ ለማድረግ እና ምጣኔ ሃብታዊ፣ ስነ ልቡናዊ እና ማህበራዊ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ለማድረግ የተዘረጋ ስርዓት ነው፡፡

የዝምድና ማካካሻ ንድፈ ሃሳብም (Compensatory kinship theory) ዋና የማተኮሪያ ነጥቡ ይህ ነው፤ በተፈጥሯዊ ዘመዶቻቸው ይደረጉላቸው የነበሩ ጥቅሞች እና ፍላጎቶች እንዳይጎሉባቸው መተኪያ ዝምድና ያስፈልጋል የሚል ነው፡፡ ስለሆነም አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጋር ዝምድና ሲፈጥር አንዱ አንዱን መርዳትን፣ መተባበርን፣ አብሮ መብላትና መጠጣትን፣ ጨዋታን እንዲሁም ፅድቅን በመፈለግ ነው፡፡ ስለሆነም በውይይቱ እንደተነሳው መረዳጃና መጠቃቀሚያ መንገዶች ደግሞ በጉልበት በመተጋገዝ፣ በገንዘብ በመረዳዳት እና በማህበራዊ ጉዳዮች በመጠያየቅ ይገለፃሉ፡፡ ከላይ የተነሳው ሃሳብ ዋና ጭብጡ ዝምድና ሲፈጠር አስፈላጊነቱና ጥቅሙ በሁለቱም ዝምድና መስራቾች በኩል ስለሆነ በዝምድና ውስጥ የጋራ ጥቅም (mutual benefit) ጎልቶ የሚታይ መሆኑ ነው፡፡ ዝምድና እርስ በእርስ መደጋገፊያ፣ መረዳጃ እና መጠቃቀሚያ መንገድ ነው፡፡ ሃብት ያለው በሃብቱ፣ ሃብት የሌለው

በጉልበቱ እንዲረዳዱ በማሰብ የሚፈጠሩ ዝምድናዎች አሉ። ምንጮችም ይህንኑ የሚደግፉ ሲሆኑ ሃሳቡ "ዝምድና በመኖር ውስጥ መጋራት ነው" በሚሉት በእነ Kuper (2018) እና Sahlins (2013) ሃሳብ ተደግፎ የቀረበ ነው።

ችግር መፍቻነት እና ማህበራዊ ግንኙነትን ማጠንከሪያነት፡- ዝምድና በሌላ በኩል ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ ችግር ሲደርስ ተባብሮ መፍቻነት እና በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ መገናኛ መንገድ ነው። ይህን ሃሳብ አስመልክቶ ካሳሁን መስፍን 27/02/2016ዓ.ም ባደረግኩት ቃለ መጠይቅ የሚከተለውን ሃሳብ ሰጥተዋል፡- "ዝምድና ማለት ደስ የሚል ያለውን ችግር ሁሉ የምትነጋገሪበት ነው" ይላል። ደስ የሚል ሲል በማህበረሰቡ ዘንድ የዝምድናን አዎንታዊነት፣ ጥሩ እይታ ያለው መሆኑን የሚገልፅ ሲሆን ዘመድ ሲጎዳ የሚረዳዱበት፣ ችግር ሲደርስ ተሰባስቦ መወያያ፣ መነጋገሪያ እና ወደ መፍትሄ መሄጃ መንገድ ሆኖ የሚያገለግል መሆኑን የሚገልፅ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ወለላው ዘሪሁን በቃለ መጠይቅ (28/08/2015ዓ.ም) "ድንግር ችግርዳኪ ያኻ ድስቲዳ ታምትኝኚስ፣ ቼጌርስቱኽስ ጉሽፅኝየማ፣ አሜትባልስ ኚስኚ እቒትኖማ አብራ ዝኩኝያኽ" (ዝምድና በችግር እና በደስታ ጊዜ ለመገናኜት፣ የአመት በዓል አብሮ ለመብላት እና ለመጠጣት የሚጠቅም ነው)። በማህበረሰቡ ውስጥ አብሮነትን የሚሹ ብዙ አይነት የችግርና የደስታ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች አሉ። ስለሆነም ይህ ሃሳብ ችግርን እንደ ችግር አብሮ የሚካፈል፣ ደስታን እንደ ደስታ የሚጋራ፣ በዓል ሲደርስ ጨዋታን የሚያደምቅ፣ አብሮ የሚበላ የሚጠጣ ዘመድ ነው የሚል አንድምታ አለው። ይህ ሃሳብ Read (2018) ዝምድና ከተለያዩ ሰፋፊ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው ብሎ በገለፀው ሃሳብ ተደግፎ የቀረበ ነው።

ሌሎች መረጃ ሰጪዎቼ ደግሞ ምንነቱን ከአፈጣጠር ስርዓቱ ጋር በማብራራት ሃሳብ ሰጥተዋል። አቶ አሳዬ በቃለ መጠይቅ (12/09/2015ዓ.ም) እንዲህ ይላል፡- "ዝምድና በተለያየ መንገድ ይገለፃል፣ የዘር ግንድ አለ፣ ከዘር ግንድ ውጪ ደግሞ የተለያዩ ዝምድና የሚፈጥሩ ነገሮች አሉ፣ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የሚፈጥሩ ነገሮች አሉ፣ ለትስስር፣ ለግንኙነት፣ ለእድገት፣ ለኑሮ ተብሎ የጡት ልጅ እንደ ልጅ ይቆጠራል፣ ክርስትና ማንሳት እንደ ልጅ ይቆጠራል።" በዚህ ሃሳብ ውስጥ የሚከተሉት ይዘቶች ተነስተዋል። የመጀመሪያው ዝምድና በዘር እና በሌሎች ባህል በሚፈጥራቸው የዝምድና ስርዓቶች የሚፈጠር መሆኑን የሚገልፅ ነው።

ሌላው ዝምድና ትስስር መፍጠሪያ፣ ግንኙነትን ማጠንከሪያ፣ በኢኮኖሚ መበልፀጊያ በአጠቃላይ ኑሮን ለማሻሻል ተብሎ የሚፈጠር

መሆኑን የሚገልፅ ነው (ይህ ሃሳብ በመረጃዎችና በማስረጃዎች ተደግፎ በምክንያቱ ክፍል ተብራርቶ ቀርቧል)።

ከዚህ በተጨማሪ አቶ አሳዬ ከዝምድና መፍጠሪያ ስርዓቶች ውስጥ የስጋ ዝምድናን ጡት መጣባትን እና ክርስትና መናሳትን ጠቅሰዋል። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ዝምድና በስጋ፣ በጋብቻ እና በጡት መጣባት የሚመጣ ስርዓት መሆኑን ገነቴ አድማሴ በቃለ መጠይቅ (19/10/2016 ዓ.ም) አስረድተዋል። ሃሳቡ ዝምድና በመወለድ እና በሌሎች ባህል በሚፈጥራቸው ስርዓቶች የሚመጣ እንደሆነ የሚጠቁም ነው። መረጃ ሰጪዎች እንዳስረዱት በዚህ ማህበረሰብ ዘንድ የዝምድና ትርጓሜ ስነ ህይወታዊ እና ማህበራዊ ይዘት ያለው ሲሆን ፍቅር፣ ሰላም፣ መረዳዳት፣ መጠቃቀም፣ አብሮ መብላት፣ መጠጣት እንዲሁም ግንኙነት ማጠንከሪያነት በሚሉ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ነው። ስለሆነም ዝምድና በዚህ ማህበረሰብ ዘንድም የጋራ ስለሆነ በችግር፣ በደስታ፣ በጥቅም እና በፍላጎት መጋራትን የሚሰብክ ነው። ስለሆነም ዝምድና አብሮነትን፣ መረዳዳትን፣ መገናኜትን፣ መተሳሰብን ወዘተ. የሚገልፅ ነው።

የአዊ ማህበረሰብ የዝምድና አፈጣጠር ስርዓት በምሁራን ክርክር ውስጥ በሶስተኛ ደረጃ ከተነሳው Gellner (1958); Crossman (2019) and Schneider (2004) kinship is both biological and social ካሉት የሚመደብ ነው። ማህበራዊ ዝምድናዎች ከላይ እንደተጠቀሙት እንደ ጡት መጣባት፣ ክርስትና መናሳት፣ የአደራ ልጅ ማሳደግ ያሉ የዝምድና ስርዓቶች ናቸው። እነዚህ የዝምድና ስርዓቶች የሰዎችን ምጣኔ ሃብታዊ፣ ማህበራዊ እና ስነ ልቡናዊ ችግሮች በመፍታት በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ ናቸው። ምጣኔ ሃብታዊ ችግር ብቻውን መነሻ ሆኖ ዝምድና የሚፈጠርባቸው ስርዓቶች አሉ። ሰው ለማግኜት እና ማህበራዊ ህይወትን ለመመስረትም እንደዚሁ ትልቅ ጉዳይ ሆኖ ዝምድና ይፈጠራል። ማህበራዊ ዝምድናዎች ኢኮኖሚያዊ ችግርን በመፍታት፣ ማህበራዊ ህይዎትን በመመስረት፣ ስነ ልቡናዊ ጉዳትን በመጠገን፣ ሰው ከማጣት፣ ገንዘብ ከማጣት ችግር በማስወጣት ስነ ልቡናዊ ጉዳትን በመጠገን እንዲሁም ደግሞ እንደዚህ አይነት ልማዶችና ባህላዊ ስርዓቶች እንዲቀጥሉ በማድረግ በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ ናቸው። ስለሆነም ማህበራዊ ዝምድናዎች ከተፈጥሯዊው ዝምድና ባልተናነሰ ለማህበረሰቡ ህልውና ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ ናቸው።

ዝምድና ሲፈጠር በእያንዳንዱ የዝምድና መፍጠሪያ ስርዓት ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎች ማህበራዊ ደረጃ ግምት ውስጥ ይገባል። ማንኛውም ሰው በማንኛውም የዝምድና ስርዓት እንዲሁ ዝም ብሎ

አይሳተፍም፡፡ ሃይማኖት፣ ምጣኔ ሃብታዊ ሁኔታ እና ሰዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸው ማህበራዊ ደረጃ ግምት ውስጥ ይገባል፡፡ ለምሳሌ ጡት መጣባት የዝምድና ስርዓት በአብዛኛው የሚፈፀመው በሃብቱ፣ በዘመድ አዝማድ ብዛት፣ በእድሜ እንዲሁም ደግሞ በሰዎች ዘንድ ባለው ተቀባይነት ከፍ ያለ ሰው እና በምጣኔ ሃብት፣ በእድሜ እና በዘመድ ካነሰ ሰው ጋር ነው፡፡ እንደጡት መጣባት የዝምድና መፍጠሪያ ስርዓት ሁሉ ሌሎች የዝምድና ስርዓቶችም የተለያዩ ፍላጎቶችን፣ ችግሮችን፣ ጥቅሞችን ወዘተ. መሰረት አድርገው የሚፈጠሩ ስለሆኑ የሰዎች ማንነት የዝምድና መፍጠሪያ ስርዓቱን ይወስነዋል፡፡

## የዝምድና መፍጠሪያ ምክንያቶች (ሰበቦች)

ዝምድና በአዊ ማህበረሰብ ዘንድ ዝም ብሎ የሚፈጠር አይደለም፡ ፡ ከኋላ የሚገፉ የተለያዩ ፍላጎቶች እና ጥቅሞች አሉ፡፡ እነዚህ ፍላጎቶች እና ጥቅሞች በሚከተሉት ጉዳዮች ዙሪያ የሚያርፉ ናቸው፡፡

## ንግድና አስተማማኝ የንግድ ከባቢ ለመፍጠር

በአዊ ማህበረሰብ ዘንድ ዝምድና እንዲፈጠር ምክንያት የሆነው አንዱ ጉዳይ ንግድና አስተማማኝ የንግድ ከባቢ ለመፍጠር ነው፡፡ ማህበረሰቡ ከእርሻ ስራ በተጨማሪ በንግድ ስራም ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ የመነገድ ልምድ አለው፡፡ ለንግድ የሚጠቀሙባቸው እንስሳት ከብት፣ ፍየል፣ በግ እና አህያ ናቸው፡፡ ንግድ የሚነግዱት ከቅርብ ቦታ ብቻ አይደለም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ እንስሳትን የሚነግዱት ከአካባቢያቸው ራቅ ብለው በመሄድ ነው፡፡ ሩቅ ወደ ሆነ ቦታ በሚሄዱበት ጊዜ ደግሞ ማረፊያ፣ መጠጊያ ከለላ የሚሆናቸው ሰው ያስፈልጋቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ያለው ብቸኛው አማራጭ ደግሞ ዝምድና መፍጠር ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ተሳታፊ 1 [4] በቃለ መጠይቅ (27/02/2016ዓ.ም) እንዲህ ይላሉ፡- “ጌቤላ ካኑስ ካኑስ ሲፍስትናናጊ እቻ ጌቤል ያኹኒ ናካ ካሳታ አንጎፃኹዒ ይታላ አለማየሁ እንግዳ ኾዳ ካሳታ ቻ፡፡ እሊኩስኾዳ ታቒኹዳ ካቱኒ አቲንካማ ታራታርኘኛና፡፡ አቒ እምኔት ዝኮላ እሊው ዲቮ ዔጌራማ ካንትስቴ፡፡ ይታላስሆዳ ክዒ ጀርታ አቓታ ሼውዴስ ዴስኔይ፡፡” (ገበያ ስንሄድ ስንሄድ ተሸኝተን ነው የምናድረው፣ ለነገ ገበያ ከሆነ የምሄደው እንደዛሬ ሄጄ ማደር አለብኝ እኔ አለማየሁ እንግዳ የጡት አባቴ ነው፤

[4] ይህ ጥናት ካለው ወቅታዊ ችግር አንፃር በብዙ ችግሮች እና ፈተናዎች ውስጥ ሆኖ የተሰራ ነው፡፡ ስለሆነም አንዳንድ መረጃ ሰጪዎቹ ስሜንም እንዳትጠቅሺ፣ ፎቶም እንዳታነሺ፣ ድምፄንም እንዳትቀጂ ዝም ብለሽ በማስታወሻ ደብተር መፃፍ ትችያለሽ ብለዋል፡፡ እኔም የመረጃ ሰጪዎቼን ግላዊ ሚስጥር ለመጠበቅ ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ መረጃ ሰጪዎቼን ተሳታፊ አንድ፣ ተሳታፊ ሁለት … በሚል ሰይሜ ተጠቅሜበታለሁ፡፡

ከሌላ ብትሄጂ ማነው የሚል ጥርጣሬ ይኖራል፣ ሰው እምነት አይኖረውም ሌላ ይመስለዋል፡፡ ከእሱ ቤት ግን ምን ብየ ልንገርሽ እንደ ልጆቹ ሁኜ እንደልቤ ነው የምሆነው)፡፡ ተሳታፊ 1 ከላይ እንዳነሱት ከአካባቢው ራቅ ብሎ ሄዶ ንግድ የሚነግድ ሰው ጠዋት ለገበያ እንዲደርስ ዛሬ ሄዶ ማደር ይጠይቃል፡፡ ሄዶ ለማደር ደግሞ ማደሪያ፣ መጠጊያ፣ ማረፊያ ሰው ያስፈልጋል፡፡ ተሳታፊ አንድ ያለ ስጋት ተንቀሳቅሶ ለመነገድ ቀድሞ ያመቻቸው ማረፊያውን ነው፡፡ ይህን ያደረገውም ከአቶ አለማየሁ እንግዳ ጋር ጡት ተጣብቶ ዝምድና በመፍጠር ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን በማህበረሰቡ ዘንድ ማን ነው? ምን ሊሰራ መጥቶ ነው? ከየት መጥቶ ነው? የሚሉ ብዙ ጥያቄዎች እና መጠራጠሮች ይመጡበታል፡፡ ስለሆነም በማህበረሰቡ ዘንድ አለመታመንን እና ጥርጣሬዎችን ለማስወገድ የግድ ከማህበረሰቡ አባላት ጋር መቀላቀል እና መመሳሰል ያስፈልጋል፡፡ ተሳታፊ አንድም እነዚህ ጥያቄዎች እንደሚመጡበት ስለሚያውቅ ከአቶ አለማየሁ ጋር በጡት መጣባት የዝምድና ስርዓት ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅሏል፡፡ አቶ አለማየሁ በአካባቢው የታወቀ፣ የተመሰገነ በምጣኔ ሃብቱም ከሌሎች የተሻለ የሚኖር ሰው ነው፡፡ በመሆኑም የአቶ አለማየሁ የጡት ልጅ ነው ወይም አበልጅ ነው መባል ለተሳታፊ አንድ ትልቅ ስም ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ስም ይህ ሰው ሌባ ነው? ሰላይ ነው? ወሳጅ ነው? መልዕክተኛ (የመጥፎ ነገር መልዕክተኛ) ነው? ወይስ ምንድን ነው የሚሉ ጥያቄዎች ወደ እሱ እንዳይመጡበት ከለላ የሚሆነው ስም ነው፡፡ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በዝምድና ተሳስሮ ማንነቱን የእነ እከሌ ወገን፣ ዘመድ ነው ማስባል በአካባቢው በነፃነት እንዲንቀሳቀስ እና የፈለገውን ስራ እንደልቡ እንዲሰራ የሚረዳው ነው፡፡

ማህበረሰቡም ደግሞ በሚኖርበት አካባቢ አዲስ ሰው ሲያይ እንዲህ አይነት ጥንቃቄዎችን ማድረጉ አካባቢው እንዳይረበሽ፣ ሃብት ንብረቱ እንዲጠበቅ፣ ሚስቱና ልጆቹ እንዳይደፈሩበት፣ ቤቱ እንዲጠበቅለት ይረዳዋል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን በዚህ ሰው ላይ ብዙ ችግሮች ይመጣሉ፡፡ ስለሆነም አንድ ነጋዴ እንደዚህ አይነት ስራ ከመጀመሩ በፊት የአካባቢውን ማህበረሰብ እይታ እና አመለካከት መቀየር ላይ ብዙ ጥረቶችን ያደርጋል፡፡ ሌባ ይሆን ሰላይ ይሆን ወይስ ምንድን ነው የሚለውን ማንነቱን እሱማ የእገሌ የጡት ልጅ ነው ወይም እሱማ የእገሌ አበልጅ ነው ወደ ሚለው ማንነት መቀየር ይኖርበታል፡፡ ማንነቱን ይፋ አድርጎ ይሄንን ስም ካገኘ በኋላ ከተለያዩ ጥርጣሬዎች እና አለመታመኖች ነፃ ስለሚወጣ በአካባቢው እንደልቡ ተንቀሳቅሶ የሚፈልገውን እንስሳም ሆነ ቁሳቁስ መግዛት፣ መሸጥና መለወጥ ይችላል፡፡

አንድ ሰው ለንግድ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ከሄደበት አካባቢ የማህበረሰቡ አባላት ውስጥ የስጋ ዘመድ ከሌለው አብዛኛውን ጊዜ የሚዛመደው በጡት መጣባት እና በክርስትና መናሳት የዝምድና መፍጠሪያ ስርዓቶች ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እነዚህ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው የሚነግዱ ሰዎች ከሚኖሩበት አካባቢ ትዳር ያልያዙ ከሆኑ በጋብቻ ይዛመዳሉ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ በ04/04/2016ዓ.ም ከአቶ የኔ አለም በሪሁን ጋር ባደረግኩት ቃለ መጠይቅ እንዲህ ይላሉ፡“እምፐላኒ እምፐላኒኪ ሚፃያሱ ያኹኒጊ ቱትኘኚስ ድንግርቴ፡፡” (“አንዳንድ ጊዜ ግን ትዳር ያልያዘ ከሆነ በጋብቻ ይዛመዳል)”፡፡ አቶ የኔ አለም እንደገለፁት ይህ ብዙ ጊዜ የሚደረግ አይደለም፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ለስራ የሚንቀሳቀሱ ሰዎች ከሚኖሩበት አካባቢ ትዳር መስርተው ልጆች ወልደው ኑሯቸውን ለማስተካከል ብቻ ከቦታ ቦታ ተዘዋውረው ሰርተው ለማደር የሚጥሩ ሰዎች ናቸው፡፡ ስለሆነም በአብዛኛው ከጋብቻ ውጪ በሆኑት ጡት መጣባት እና ክርስትና መናሳት ዝምድና ፈጥረው ለስራ ከፈለጉት አካባቢ ማህበረሰብ ጋር ይቀላቀላሉ፡፡

በአዊ ማህበረሰብ ዘንድ ንግድ በሁለት መንገድ ዝምድና እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ አንደኛው በወዳጅነት ከሚፈጠር ዝምድና ጋር ተያይዞ ሻጭ እና ገዥ በመሆን በደንበኝነት ተነስቶ የሚፈጠር ዝምድና ነው፡፡ ወርቅነሽ ምናዬ በቃለ መጠይቅ (03/04/2016ዓ.ም) እንዲህ ትላለች፡- “ወዳጅ የእናት ልጅ ማለት ነው፣ እንዲያውም የእናት ልጅ የማያደርገውን ነው ወዳጅ የሚያደርገው፡፡” በዚህ ሃሳብ ላይ ወዳጅ የተገለፀበት መንገድ የዝምድና ከፍታውን ወይም ቅርበቱን በሚገልፅ መልኩ ነው፡፡ በተጨማሪም ከጥቅም ጋር አያይዛ ወዳጅ ከእናት ልጅ የበለጠ የሚረዳ፣ የሚጠቅም መሆኑን አንስታለች፡፡ ወዳጅ የችግር ጊዜ ደራሽ፣ ያለ አራጣ[5] አበዳሪ፣ሲቸግር ሰጪ በአጠቃላይ በችግር እና በደስታ ጊዜ ቀድሞ የሚደርስ ሰው ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ከላይ እንደተነሳው ከመኖሪያ ቦታቸው ርቀው ወደ ሌላ ቦታ እንስሳትን እና ቁሶችን መነገድ ሲሄዱ ማረፊያ፣ መጠጊያ በሚል ከሚሄዱበት አካባቢ ሰዎች ጋር ዝምድና እንዲፈጥሩ ስለሚያደርግ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ አሳዬ አንተነህ በቃለ መጠይቅ (09/09/2015ዓ.ም) “ሰዎች ለንግድ በእግር በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ በወዳጅነት ንግድ ዝምድና ይፈጠራል” ይላል፡፡ ስለሆነም በዚህ ማህበረሰብ ዘንድ በንግድ አማካኝነት ምጣኔ ሃብታዊ ፍላጎትን ለማሟላት መፈለግ ዝምድና እንዲፈጠር አንዱ ምክንያት ነው ማለት ነው፡፡

---

[5] አራጣ ማለት ወለድ ማለት ሲሆን ሃሳቡን የወሰድኩት በቡድን ተኮር ውይይት ባገኘሁት መረጃ መሰረት ነው፡፡

## ከእንግዳነት (ከአዲስነት) ስሜት ለመውጣት

ሌላው በአዊ ማህበረሰብ ዘንድ ዝምድና እንዲፈጠር ምክንያት የሆነው ጉዳይ ከእንግዳነት ስሜት ለመውጣት ካለ ፍላጎት ነው። አንድ ሰው በተለያዩ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ምክንያቶች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ይፈልሳል። አንድም በአካባቢው ፀጋ በመማረክ፣ በፀጥታ ችግር ምክንያት በመፈናቀል፣ በአየር ንብረት አለመመቸት ምክንያት እንዲሁም ዝምድና ለመፍጠር በመፈለግ ሩቅ ወደ ሆነ ቦታ ሊሄዱ ይችላሉ። ከሌላ ቦታ ተፈናቅሎ የመጣ ሰው ደግሞ ከሄደበት አካባቢ የራሱ የሚለው ዘመድ አዝማድ፣ መተዳደሪያ መሬት፣ መጠለያ እና ሃብት ንብረት የለውም። በዚህ ጊዜ ዘመድ አዝማድ እንዲያገኝ፣ መጠለያ እንዲኖረው እና መተዳደሪያ መሬት እንዲሰጠው ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር መቀላቀል ይፈልጋል። የሚቀላቀለው ደግሞ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በመዛመድ ነው። የአዊ ማህበረሰብ እንግዳን ሰው በአብዛኛው ከማህበረሰቡ ጋር የሚያዛምድበት መንገድ በጡት መጣባት የዝምድና ስርዓት ነው። ምክንያቱም ጡት መጣባት የዝምድና ስርዓት ባለፀጋን እና ብዙ ዘመድም ሆነ፣ ሃብት ንብረት የሌላቸው ሰዎችን የሚያገናኝ ስርዓት ነው። እንግዳ ሰዎች ደግሞ በተለያዩ ችግሮች ምክንያት አካባቢያቸውን ለቀው የሚመጡ ስለሆኑ ምንም ነገር የላቸውም። ስለሆነም እንደ አንድ የማህበረሰብ አባል ሊኖሩት የሚገቡ ነገሮችን ለማሟላት ሲል ከአካባቢው ባለፀጋ ጋር በጡት መጣባት የዝምድና ስርዓት መዛመድ የግድ ይሆናል። ፈጠነ የትዋለ በ29/02/2016ዓ.ም ባደረግኩት ቃለመጠይቅ የሚከተለውን ይላሉ፡- "ሃይሉ አጋዠ አንን ፃኹቪ ይታላህ። ፋግታ ታቓ ታሁኒጊ አንዴስኽ አንቱህ። አሬሳውሳ ብቴ ክምካዋ እያማ ኻኖ ፍሽፁኽ ኻያህ።" (ሃይሉ አጋዤ የጡት አባቴ ነው፣ ፋግታን ታውቂው ከሆነ ከዚያ ነው የመጣሁት፣ የማርሰው መሬት ከብት ሰጥቶ ቤት ያስያዘኝ እሱ ነው።)

አቶ ፈጠነ ከፋግታ ወደ ጓንጓ ወረዳ ሄዶ የሚኖር ለጓንጓ ወረዳ ማህበረሰብ እንግዳ የሆነ ሰው ነው። ይህ ሰው ጓንጓ ወረዳ ሲመጣ የኔ የሚለው ዘመድም የሚተዳደርበት ሃብትም አልነበረውም። በዚህ ጊዜ ከአካባቢው የተሻለ የሚኖርን ሰው አጥንቶ መዛመድ ነበረበት እና ሃይሉ አጋዤን ጡት በመጣባት ተዛምዶ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ተቀላቀለ። ሃይሉ አጋዤ ደግሞ በአካባቢው የተመሰገነ ሃብት ንብረት ያለው በዘመድ የተከበበ ስመ ጥር ሰው ነው። ከእሱ ጋር ጡት በመጣባቱም ብዙ ጥቅሞችን አግኝቷል። የመጀመሪያው የእኔ የሚለውን የሚኮራበትን በክፉ በደጉ የሚደርስለትን የጡት አባት ዘመድ አገኘ፣ ሌላው ደግሞ አርሶ የሚጠቀምበት መሬት እና የሚያርስበት ከብት ተቀበለ። ከዚህ በኋላ እሱ አንድ የአካባቢው ማህበረሰብ አባል ስለሆነ በተለያዩ

ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ ጉዳዮች ላይ እንደልቡ መሳተፍ ይችላል፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ አንድ ሰው እንግዳ ወይም አዲስ ከሆነ ከእንግዳነቱ ጋር ተያይዞ የሚመጡ ብዙ ችግሮች አሉ፡፡ ሰው ማፍራት ወይም መዛመድ ትልቅ ሃብት ነው፡፡ ሃዘንን ሃዘን የሚያደርገው፣ ደስታን ደስታ የሚያደርገው፣ ችግር ቢደርስ ዋስ ጠበቃ የሚሆነው ወገን ዘመድ ነው፡፡ ስለሆነም እንግዳ ሰዎች ከሄዱበት አካባቢ እንግዳ ወይም ባዕድ ሆነው መቀመጥ አይፈልጉም፡፡ ቶሎ ጠጋ ብለው የአካባቢው ማህበረሰብ አባል መሆንን ያስቀድማሉ፡፡ ምክንያቱም ከእንግዳነት ጋር ተያይዘው የሚመጡ ጎዶሎዎች የሚሞሉት ዝምድና በመፍጠር ከማህበረሰቡ ጋር መቀላቀል ሲችሉ ነው፡፡ እንግዳ ሰዎች በአብዛኛው የሰው እና የኢኮኖሚ ችግር ያለባቸው ናቸው፡፡ ዝምድና የሚፈጥሩትም ከአካባቢው ባለ ፀጎችና ስመ ጥር ከሆኑ ሰዎች ጋር ነው፡፡

ሰዎች ወደ ሌላ ቦታ ሄደው እንግዳ እንዲሆኑ የሚያደርጓቸው ምክንያቶች አንድም በአካባቢያቸው አለመመቸት ምክንያት ወደ ሌላ ቦታ ሄደው ለመኖር ሁለተኛም ደግሞ ስራ ሰርቶ ለመመለስ ነው፡፡ ስለሆነም ለሄዱበት አካባቢ ማህበረሰብ እንግዳ የሚሆኑባቸው ጊዜያት ለቀናት፣ ለሳምንታት፣ ለወራት ወይም ኑሯቸውን ከዚያው ለማድረግ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም የቆይታ ጊዜያቸው የሚወሰነው ሰዎች ይዘውት እንደሄዱት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም ሰዎች አዘውትረው ከሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች ካሉ ማህበረሰቦች ጋር ዝምድና መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ማህበረሰቡ እንግዳ ሰው በአካባቢው ሲሄድ ብዙ ጥርጣሬዎች አሉበት፡፡ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ አቶ አሳዬ አንተነህ (ቃ.መ፣ 02/04/2016ዓ.ም) የሚከተለውን ሃሳብ ሰጥተዋል፡፡

ሂደሽ ለማደር ዘመድ መፍጠር አለብሽ፡ የሚንቀሳቀስበት ቦታ ላይ የሆነ ነገር መዋቅር ካልዘረጋ እንግድነት እንኳን ቢሄድ ጥርጣሬ ያመጣል፡፡ ሊሰርቅ መጥቶ ነው፤ለሌላ ጉዳይ መጥቶ ነው እእእእ.. በሚል ለአንድ ቀን አድሮ ለመሄድ እንኳን ለእግዚዓብሄር እንግድነት በስጋት ጥበቃ ተደርጎ ተጠንቅቆ ነው ያ ሰውየ እስኪሄድ የእግዚዓብሄር እንግድነት አይከለከልም፤ ነገር ግን የእምነት ጉዳይ ግን ያጠራጥራል፡፡ ከየት መጣ? እሱ አንዱን ቦታ ይጠራል፤ ምሄደው ወደዚህ ነው ውሃ ሞልቶብኝ ነው፣ መሽቶብኝ ነው እና ለእግዚዓብሄር አሳድሩኝ ይላል ከዛ ሚበላ ሚጠጣ ተሰጥቶት ከዚያ የሆነ ቦታ ተሰጥቶት በንቃት ነው ቤተሰቡ የሚተኛው ያን ቀን ያ ሰው እስኪሄድ ድረስ፡፡

ከላይ በተገለፀው ሃሳብ ተብራርቶ የቀረበው ማህበረሰቡ እንግዳ ሰውን ዝም ብሎ እንደማይቀበል፣ ብዙ ስጋቶች እንዳሉበት እና እንግዳ ሆኖ የሚሄደው ሰው ምንም አይነት ምክንያት ቢያቀርብ የእገሌ ዘመድ

ነኝ ካላለ በስተቀር እንደማይታመን የሚያመለክት ነው፡፡ ሃሳቡ እንደሚያስረዳው ማህበረሰቡ ማብላት ማጠጣት ላይ ችግር የለበትም፡፡ ነገር ግን የማያውቀውን፣ ያልተዛመደን ሰው ሙሉ እምነት ኖሮት አያሳድረውም፡፡ ከጥቅሱ ውስጥ "በስጋት ጥበቃ ተደርጎ ተጠንቅቆ ነው ያ ሰውዬ እስኪሄድ" የምትለውን ሃሳብ ብንወስድ የማያውቀው ሰው አሳድሩኝ ብሎ እንኳን ተፈቅዶለት ቢያድር አሳዳሪው ስጋት አለበት፤ ይሰርቅ ይሆን ይደፍር ይሆን ወይስ ምን ሊያደርግ ይችል ይሆን በሚል ከፍተኛ ጥንቃቄ ተደርጎ ያን ቀን እንቅልፍ አይተኛም፡፡ ጥበቃ ሲደረግ ይታደራል፡፡ ስለሆነም ሰው በሙሉ ልቡ ያለ ፍርሃት እና ስጋት ለማደርም ለማሳደርም ዝምድና መፍጠር ወሳኝ ነው ማለት ነው፡፡

## ከድህነት ለማምለጥ

በአዊ ማህበረሰብ ዘንድ ድህነትም ዝምድና እንዲፈጠር ሰበብ ወይም ምክንያት ይሆናል፡፡ ድህነት ከዚህ ማህበረሰብ አንፃር በሁለት መንገድ ይተረጎማል፡፡ አንደኛው ከምጣኔ ሃብት ችግር አንፃር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከወገን ዘመድ ማጣት አንፃር ይገለፃል፡፡ ስለሆነም ከማህበረሰቡ አባላት ውስጥ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚኖሩ ሰዎች ቤተሰብ ማስተዳደር ሲያቅታቸው ልጆቻቸውን በአደራ መልክ ይሰጣሉ፡፡ ምንም አይነት መሬት የሌለው ሰው ደግሞ የሚታረስ መሬት ለማግኘት ሲል፣ ገንዘብ ወይም እንስሳት ለመቀበል ሲል ከባላባት ጋር ጡት ይጣባል፣ የሰው ደሃ ወይም ዘመድ አዝማድ በዙሪያው ሲያጣ ደግሞ ዘመደ ብዙ ከሆነ እና ስመ ጥር ከሆነ ሰው ጋር ጡት ይጣባል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ የሰው፣ የዘመድ ደሃ መሆን ከምጣኔ ሃብታዊ ድህነት ባልተናነሰ ሰዎችን ለስነ ልቡናዊ ጉዳት የሚዳርግ ነው፡፡ ስለሆነም በተለያዩ ማህበራዊ እና ምጣኔ ሃብታዊ ጉዳዮች ለመሳተፍ ከሰው መጨመር የግድ ይሆናል፡፡ ይህን ጉዳይ በቀጥታ በሚመለከት አቶ ፈለቀ አለሙ በቃለ መጠይቅ (27/02/2016ዓ.ም) እንደሚከተለው ሃሳብ ሰጥተዋል፡- "መኮንን እንግዱን እዚህ ሻሽና [6]ጡት አባት አድርጌ በጣም እና በጣም ከአባቴ በላይ እርዳታ ያደረገልኝ ነው መጀመሪያ ከብት ሰጥቶኝ ሸጥሁና የስፌት መኪና ገዝቸ እስካሁን አለች፣ እሱ ብቻ አይደለም እሱ ሲሞት ለእሱም ሃብት ስጡት ተብየ ከልጆች እኩል ሃብት ወስጃለሁ፡፡" በዚህ ሃሳብ ብዙ ዘርዝር ያሉ መልዕክቶች ተላልፈዋል፡፡ ቀደም ብሎ በተገለፀው ሃሳብ ጡት መጣባት የዝምድና ስርዓት ምጣኔ ሃብታዊ ችግር ያለባቸው እና ባለሃብቶች የሚዛመዱበት የዝምድና ስርዓት እንደሆነ ተገልጧል፡፡ ስለሆነም በዚህ ሃሳብ አንደኛ

---

[6] "ሻሽና" ከጓንጓ ወረዳ ቀበሌዎች ውስጥ አንዷ ናት፡፡

ጡት ጠቢው ሃብት ተቀባይ፣ አጥቢው ሰጪ መሆኑ በምጣኔ ሃብት ያላቸውን ማህበራዊ ደረጃ የሚያመለክት ሲሆን ጡት ጠቢው ከአጥቢው ዝቅ ያለ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ አቶ መኮንን እንግዱ የጡት ልጁን አቶ ፈለቀን ቤት እንዲይዝ መሰረት አስይዞታል፡፡ ከልጅ እኩል መቆጠሩን ለማመልከት የጡት አባት ሲሞት ለጡት ልጁ ለአቶ ፈለቀ ከልጆች እኩል እንዲካፈል ስለተናዘዘ (ስለተናገረ) በውርስ ጊዜ የጡት ልጅ ከሌሎች ልጆች እኩል ተካፋይ ሆኗል፡፡ ትንታኔው እንደሚመራን በዝምድና ስርዓት ውስጥ “Resource sharing concept” ሃብት ንብረትን ማካፈል ፅንሰ ሃሳብ ጎልቶ የሚታይበት ነው፡፡ ምንም የሌለው ደሃ ሰው ከባለ ፀጋ ጋር የሚዛመደው ሃብት ንብረት ለመካፈል ነው፡፡ ስለሆነም ማካፈል፣ መካፈል የሚሉ ፅንሰ ሃሳቦች በዝምድና ስርዓት ውስጥ የሚታዩ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ከላይ እንደተጠቆመው ጡት መጣባት እና የአደራ ልጅ ተቀብሎ ማሳደግ ከማህበረሰቡ የዝምድና መፍጠሪያ ስርዓቶች ውስጥ የሚካተቱ ሲሆን የአደራ ልጅ ማሳደግ ከማህበረሰቡ አባላት ውስጥ ልጆችን ወልደው የሚያበሏቸውና የሚያጠጧቸው ወይም የሚያሳድጉበት ሃብት ሲያንሳቸው ወይም ደግሞ ወላጆቹን በሞት ያጣን ልጅ በአደራ መልክ ሃብት ላለው እና ማስተዳደር ለሚችል የአካባቢው ባለሃብት ሰጥቶ እንዲያድጉ ማድረግን የሚመለከት ነው፡፡ የሰው ልጅ በሰው ሰራሽም ይሁን በተፈጥሯዊ ምክንያቶች ወላጆቹን ወይም ዘመዶቹን ሊያጣ ይችላል፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ዘንድ አንድ ልጅ በሰው ሰራሽ ምክንያት ከወላጆቹ ወይም ከዘመዶቹ የሚለየው በችግር፣ ማሳደጊያ በማጣት ምክንያት ነው፡፡ በተፈጥሯዊ ምክንያት ወላጆቹን የሚያጣው ደግሞ በሞት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ይህ ማህበረሰብ ደግሞ በእንደዚህ አይነት ምክንያቶች ወላጆቻቸውን ሲያጡ በምትኩ ወላጅ ሆነው ለማሳደግ በአደራ መልኩ ይቀበላሉ፣ ያሳድጋሉ፡፡ አንድ ልጅ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ እናት አባቱ፣ እህት ወንድሙ የሚሆኑት አሳዳጊዎቹ ናቸው፡፡ በዚህ ጉዳይ አቶ ገነቱ ወልዴ በቃለ መጠይቅ (27/09/2015ዓ.ም) እንዲህ ይላሉ፡-

ወላጅ አልባን በማሳደግ ቤተሰብ፣ ዘመድ መሆን አለ፣ አሁን እናት አባቱን ያጣን ልጅ እኔ ባሳድገው አባቴ ብሎ በፍፁም የእኔን ልጆች እህቴ ወንድሜ ብሎ ልጅ ሆኖ አብሮ ይኖራል በቃ፡፡ እእእ…. በርካታዎች አካባቢያቸው ላይ ሰው፣ እናት፣ አባት አጥተው የሚያስጠጋ ወገን ቢጠፋ የተሻለ ሰው ያለው ባሳድገው ለእኔም ይረዳኛል በእግዚዓብሄርም ዋጋ አገኛለሁ ብሎ ያሳድጋል፡፡

ሰዎች ተፈጥሯዊ ወላጆቻቸውን የሚያጡት አንድም በተፈጥሯዊ ነገር ሌላም ደግሞ ሰው ሰራሽ በሆነው የምጣኔ ሃብት ችግር ማሳደጊያ

ሲያጡ ነው ተብሏል፡፡ አቶ ገነቱም ወላጅ አልባ የሆኑ ህፃናትን የሚያቅፍ የሚደግፍ ከሌለ አንድ በኑሮው የተሻለ የአካባቢው ነዋሪ ወስዶ እንዲያሳድግ ይደረጋል፡፡ የተወሰደው ሰውም ሰው በዙሪያው አልነበረውምና የሰው ሃብት ያገኛል፡፡ በእናት፣ አባት፣ እህት ወንድም እንዲሁም ሌሎች በእነሱ ዙሪያ ያሉ ዘመዳሞችን ይቀላቀላል ማለት ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ እማሆይ ጉዳይ አጋሉ ተጨማሪ ሃሳብ ሲሰጡ ወላጆቿ በችግር ምክንያት ማሳደግ ያልቻሏትን ስንታየሁን ተቀብለው አስተምረው፣ ትዳር አስይዘው ለቁም ነገር እንዳበቁ አስረድተዋል (ቃ.መ 21/03/2016ዓ.ም)፡፡ ከተሰጠችበት ቀን ጀምሮ ልጅነቷም ለእማሆይ ጉዳይ አጋሉ እንደሆነ በቃለ መጠይቁ አስረድተዋል፡፡ ስለሆነም ምጣኔ ሃብታዊ እና ስነ ልቡናዊ ችግሩን የሚፈቱለትም እነዚሁ የተቀበሉት ሰዎች ናቸው፡፡ አንድ ህፃን ልጅ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የአባትና የእናቱን ቦታ ይዘው የሚያሳድጉትም እነዚህ በአደራ መልክ የተቀበሉት ሰዎች ናቸው፡፡ compensatory kinship theory (የዝምድና ማካካሻ ንድፈ ሃሳብ) በንድፈ ሃሳብ ቅኝት ክፍል እንደተነሳው ልጆች በተፈጥሯዊ ወላጆቻቸው ያገኙዋቸው የነበሩ ጥቅሞች እንዳይቀሩባቸውና በምጣኔ ሃብት፣ በስነ ልቡና እንዲሁም በማህበራዊ ህይወት እንዳይጎዱ ሌሎች አማራጭ ዝምድናዎች ተፈጥረው ያገኟቸው የነበሩ ጥቅሞች እና ፍላጎቶች እንዳይቀሩባቸው፣ እንዲሟሉላቸው መሆን አለበት የሚል ነው፡፡

በዚህ ማህበረሰብ ዘንድም ከላይ እንደተገለፀው ወላጆቻቸው በምጣኔ ሃብት ችግር እና በሞት ምክንያት ተፈጥሯዊ ወላጆቻቸው ለልጆች የሚያስፈልጓቸው ነገሮችን ማሟላት ሳይችሉ ሲቀሩ በአደራ መልክ ማሳደግ ለሚችሉ ሰዎች ሰጥተው ያጧቸውን ነገሮች እንዲያገኙ ለማድረግ ስርዓት ተዘርግቷል፡፡ የእነዚህ የዝምድና መፍጠሪያ ስርዓቶች ትልቁ አላማቸው ምጣኔሃብታዊ ችግርን መፍታት እና የሰው ደሃ የሆኑ ሰዎችን ዘመድ በማስገኜት በኩል ስነልቡናዊ ጉዳትን መጠገን ነው፡፡ ይህ ትንታኔ Alvarado (2018) እነዚህ የዝምድና መፍጠሪያ ስርዓቶች ከ1950ቹ በኋላ የጥናት ትኩረት እንዳገኙ እና ማህበራዊ እና ምጣኔሃብታዊ ችግርን በመፍታት በኩል ለማህበረሰቡ ከፍ ያለ ጠቀሜታ እንዳላቸው ገልፆ "እነዚህ የዝምድና አይነቶች በማህበረሰቡ ውስጥ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን እና በሃብት የበለፀጉ ሰዎችን በማገናኘትና የድሆችን ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ በማሻሻል በኩል አይነተኛ ጉዳዮች ናቸው"(pp.1-3) በሚል ከገለፀው ሃሳብ ጋር በቀጥታ የተገናኘ በመሆኑ በዚህ ሃሳብ ተደግፎ የቀረበ ነው፡፡

## ከብቸኝነት (ወገን አልበኝነት) ስሜት ለመውጣት

ከማህበረሰቡ አባላት ውስጥ አንዳንድ ሰዎች ብቸኛ የሆኑ ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ይህን በተመለከተ መረጌታ ላዕከ ማሪያም ቸኮል (ቃ.መ፣ 02/04/2016ዓ.ም) "የወገን ማነስ ያላቸው ሰዎች አሉ" ይላሉ፡፡ አንዳንድ ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች ዘመዶቻቸውን አጥተው ብቻቸውን የሚኖሩ ሰዎች አሉ፡፡ የሰው ልጅ ደግሞ ከማህበረሰቡ ወይም ከቡድኑ ተነጥሎ ብቻውን የሚኖር ፍጡር አይደለም፡፡ አብሮ እንዲኖር፣ እንዲቀላቀል ሁኔታዎች ያስገድዱታል፡፡ በአንድ በተዋቀረ ማህበረሰብ፣ ቡድን ውስጥ እየኖረ ሰው የለኝም ብሎ ማሰብ፣ መነጠል፣ ብቸኛ መሆን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነ ልቡናዊ ጉዳቱ ከፍተኛ ነው፡፡ከብቸኝነቱ (ከመነጠሉ) ጋር ተያይዘው የሚመጡ ጉዳቶችን ለመቀነስ ከማህበረሰቡ ጋር ሲኖር በዙሪያው ያለውን የሰው ሃይል ማስፋት ይጠበቅበታል፡፡ ችግር ቢደርስበት፣ በተለያዩ ማህበራዊ እና ምጣኔ ሃብታዊ ጉዳዮች መሳተፍ ቢፈልግ እና በስራ ጊዜ መረዳዳት ቢያስፈልገው በዙሪያው ሰው ማስፈለጉ አይቀርም፡፡ እንደዚህ አይነት ፍላጎቶችን እና ጥቅሞችን ለመሙላት ሲል የሚያደርገው አማራጭ ደግሞ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ዝምድና መፍጠር ነው፡፡ በዚህ ሃሳብ ላይ ተጨማሪ መሪጌታ ላዕከማሪያም ቸኮል በቃለ መጠይቅ (02/04/2016ዓ.ም) እንዲህ ይላሉ፡-

ዝምድና የሚያስፈልግበት ምክንያት አጋጣሚ ሆኖ አንዳንድ ጊዜ ሰው አገሩን ለቆ በሰው ሃገር ሊሄድ ይችላል፣ በሰው ሃገር በሚሄድበት ሰዓት በዚያ አገር ብቸኛ ላለመሆን በመከራም ሰው ያስፈልገዋል፤ በደስታ ጊዜም ሰው ያስፈልገዋል፣ በደስታ ጊዜም ሰው ስለሚያስፈልገው ሰውን ለማፍራት ዘመድን ለማፍራት፣ ደስታየን ደስታ ያደርግልኛል፣ መከራየንም መከራ ያደርግልኛል ሲል ሰው ለማፍራት ሲል ሄዶ ጡት ይጣባል፡፡ ብቸኛ ላለመሆን ክብረ በዓልም ሲመጣ አብሮ ቡና ይጠጣል፤ መከራ አለ ደስታ አለ ያን ያን ሁሉ ለመጋራት እንዲጋራኝ ሲል ዝምድና ይፈጥራል፡፡ በአገር ቤትም ቢሆን ደግሞ ወገነ ቀላል ሰው አለና ከደና ሰዎች አካባቢ ሂዶ ይዛመዳል፤ ለምን የሆነ ነገር እንኳን ቢመጣ እና የእከሌ ዘመዳቸው ዘራቸው ብዙ ነው ወይም ደሞ ይፈራሉ በቀበሌ ላይ፣ በአገር ላይ ታፍረው ተፈርተው ይኖራሉ ስለሚባል ከእነዚያ ሰዎች ሄዶ አበልጅ ሊሆን ይችላል፣ ጡት መጣባት ሊሆን ይችላል፣ በግቢ[7] ሊሆን ይችላል ሄዶ ይዛመዳቸዋል፡፡ ይህ የሚሆነው ምንድን ነው በሃገርም ቤት ቢሆን ጀርባው ቀላል ሰው ስላለ ከእነዚያ ሄዶ ይዛመዳል ምክንያቱ ምንድን ነው አሁንም ቅድም እንዳልሁት አንዳንድ ነገር

[7] "በግቢ" ይዛመዳል ሲል በጋብቻ ይዛመዳል ለማለት ነው፡፡

ሲመጣ ግራንት ይቆሙልኛል ሲባል ነው ለዚህ ለዚህ ነው ዝምድና የሚያስፈልገው፡፡

በዚህ ረጂም ቃለመጠይቅ የተነሱ ጉዳዮች ብዙ ናቸው፡፡ ከመጀመሪያው አካባቢ ብንመለከት "ብቸኛ ላለመሆን በመከራም ሰው ያስፈልገዋል፣ በደስታ ጊዜም ሰው ያስፈልገዋል" ከዚህ ዝቅ ብሎ ደግሞ "ብቸኛ ላለመሆን ክብረ በዓል ሲመጣ አብሮ ቡና ይጠጣል" ይላል የሰው ልጅ በተፈጥሮው ብቻውን የሚኖር ፍጡር አይደለም፤ አብሮ እንዲኖር ሁኔታዎች ያስገድዱታል፡፡ መከራ ብዙ አይነት ነው፤ ሞት አለ፣ ቤት መቃጠል፣ ሃብት ንብረት መውደም፣ በሌባ መሰረቅ ወዘተ. እነዚህን ችግሮች ሰው ብቻውን የሚቋቋማቸው አይደሉም፡፡ አይዞህ የሚለው የሚያፅናናው፣ ሃብት ንብረቱ ቢወድም የሚተካለት ሌባ ቢሰርቀው ቶሎ የሚደርስለት፣ ቤት ቢቃጠል ሮጦ የሚደርስለት ወገን ዘመድ ያስፈልገዋል፡፡ በደስታ ጊዜም ሰው አስፈላጊ ነው፡፡ አንድ ሰው ብቻውን ሰርግ አይደግስም፤ በስራ የሚያግዘው፣ ድግሱን የሚበላለት፤ ሰርጉን በጭፈራ የሚያደምቅለት ሰው ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ማህበራዊ ኑሮን ለመመስረት እና ግንኙነትን ለማጠናከር ከሰዎች ጋር ሰላማዊ ግንኙነት መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ምንጮችም "የሰው ልጅ በተፈጥሮው ማህበራዊ ነው ብቻውን የሚኖር ፍጡር አይደለም" የሚሉ ናቸው Mhaiske et al. (2016)፡፡ በሚለው ሃሳብ የተደገፈ ነው፡፡ ሌላው በዚህ ቃለ መጠይቅ የተነሳው "ወገነ ቀላል" እና "ጀርባው ቀላል" የሆነ ሰው የሚለውን እና "የእነ እገሌ ዘራቸው ብዙ ነው ወይም ደሞ ይፈራሉ[8] በቀበሌ ላይ፣ በአገር ላይ ታፍረው ተፈርተው ይኖራሉ" የሚለውን ሃሳብ ስንወስድ ወገነ ቀላል ወይም ጀርባው ቀላል ሲል ብዙ ሰው፣ ወገን፣ ዘመድ አዝማድ ብዙ የሌለው ማለት ነው፡፡ አይዞህ የሚለው፣ የሚያበረታታው ፣ የሚረዳው ሰው የሌለው ማለት ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ተደማጭነት እና ተቀባይነት ያነሳቸው ናቸው፡፡ ስለሆነም ማህበራዊ ደረጃቸው ዝቅ ያለ ነው፡፡ "እነ እገሌ ዘራቸው ብዙ ነው ታፍረው ተፈርተው ይኖራሉ" የሚለውን እንመልከት፡- ዘረ ብዙ፣ ወገነ ብዙ መሆን በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖራቸው፣ እንዲፈሩ፣ እንዲታፈሩ፣ እንዲከበሩ ሰው እንዳይደፍራቸው ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ማህበራዊ ደረጃቸው ከፍ ያለ ነው፡፡ "ግራንት[9] ይቆሙልኛል ሲልም ሄዶ ጡት ይጣባል ወይም አበልጅ ይሆናል" ይላል፡፡ ይህ ዘመደ ቀላል፣ ብቸኛ የሆነ ሰው ችግር ቢደርስ ዋስ፣ ጠበቃ፣ ከለላ እንዲሆኑት ዘመደ

[8] "ይፈራሉ" የሚለው ቃል በዚህ ጥናት ጥቅም ላይ የዋለው ጠብቆ ሲነበብ የሚሰጠው ትርጉም ነው፡፡

[9] ግራንት የሚለው ቃል ዋስ፣ ጠበቃ የሚል ትርጓሜ የያዘ ነው፡፡

ብዙ ከሆኑ ሰዎች ጋር ራሱን በዝምድና ይቀላቅላል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ሌላኛው አስረጂ በ27/02/2016ዓ.ም ከካሳሁን መስፍን ጋር ያደረግኩት ቃለ መጠይቅ ሲሆን የሚከተለውን ሃሳብ ሰጥቷል፡- "ምስክር እርጥባን ከፋግታ ስራ ፍለጋ የመጣውን ደመላሽ የትዋለ [10]ን እርሻ አስገባው፣ ጡት አጠባው፣ ሴት ዳረው አጋብቶ መሬት ሁሉ ሰጥቶ አሁን ከእኛ ጋር ነው ያለው አባ ምስክር ግን ሞተ፤ መሬት ከብት ቆርሶ ሰጥቶ የሚቀመጥበት ቦታ ሁሉ ሰጥቶት ይኖራል አሁን"፡፡ ይህ መረጃ የሚያስረዳው እንግዳ ሰዎች በጡት መጣባት የዝምድና ስርዓት ከተዛመዱ ለጡት አጥቢው ልጅ ሆኑ ማለት ነው፡፡ የሚተዳደርበት ሃብት ንብረት ሰጥቶ፣ መኖሪያውን አመቻችቶ፣ ትዳር አስይዞ ማኖር የወላጅ አባት ሃላፊነት ነው፡፡ የጡት አባትም አንድን ሰው ጡት ካጠባ ቀን ጀምሮ ከልጆቼ አልለይህም ብሎ ቃል ገብቶ ልጅ የሚያደርገው ስለሆነ የብቸኝነት ወይም ወገን ዘመድ የለኝም የሚል ስሜት እንዳይሰማው የወላጅ አባቱን ቦታ ተክቶ ያኖረዋል፣ ትዳር ያስይዘዋል፣ የሚተዳደርበት ሃብት ንብረት ይሰጠዋል፤ መኖሪያ ቦታ ሰጥቶ እንዲጎራበት እና አብሮት እንዲኖር ያደርገዋል፡፡ በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮችም እንዲሳተፍ በር ይከፍትለታል፡፡ አቶ ደመላሽ ዘመድ አዝማዶቹን ሁሉ ትቶ ስራ ለመስራት ብቻውን ወደ ጓንጓ የመጣ ሰው ነው፡፡ ጡት ከጠባ በኋላ ግን ዘመድ አግኝቶ፣ ሃብት ንብረት አፍርቶ፣ መኖሪያውን አመቻችቶ የሚኖር ሰው ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ከአቶ ዘለቀ አምባዬ ጋር በ28/10/2015ዓ.ም ባደረግኩት ቃለ መጠይቅ እንደተናገሩት ለመኖር ወደ ጓንጓ ወረዳ ሲሄድ ከአካባቢው ማህበረሰብ ውስጥ ይህ ነው የሚለው ዘመድ ስላልነበረው ከአካባቢው ማህበረሰብ አባላት ውስጥ ታዋቂና ስመ ጥር ከሆነ ከአቶ ምህረት ጓዴ ጋር በጡት መጣባት የዝምድና ስርዓት ተዛምዶ በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ጉዳዮች ላይ መሳተፍ ችሏል፡፡ እንደ ዘለቀ ሁሉ አንዳንድ ሰዎች የአካባቢውን ልምላሜ በመውደድ ወይም ለመኖር

---

[10] አቶ ደመላሽ የትዋለ ከላይ የጠቀስኩት መረጃ ሰጪዬ የአቶ ፈጠነ የትዋለ ወንድም ነው፡፡ በመጀመሪያ የመጣው ደመላሽ የትዋለ ነው፡፡ እሱ መጀመሪያ መኖሪያውን ካመቻቸ በኋላ ወንድሙን አቶ ፈጠነ የትዋለን ወደዚህ ቦታ አምጥቶ አቶ ሃይሉ አጋዠን ጡት እንዲጠባ አድርጎታል፡፡ ሁለቱን ወንድማማቾች በአቶ ካሳሁን መስፍን ጥቆማ መሰረት ያገኘኋቸው ለጓንጓ ወረዳ እንግዳ የሆኑ አሁን ግን በጡት መጣባት የዝምድና ስርዓት ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው በተሰጣቸው ሃብት ንብረት መሰረት የራሳቸው ባድማ መስርተው አንድ የማህበረሰብ አባል ሆነው የሚኖሩ ሰዎች ናቸው፡፡ በትንታኔው እንደተገለፀው አቶ ፈጠነ የትዋለን በአካል አግኝቼ ቃለ መጠይቅ አድርጌያለሁ፡፡ አቶ ደመላሽ የትዋለን ግን በሁኔታዎች አለመመቻቸት ምክንያት ባለማግኘቴ በቅርብ ጎረቤቱ በነበረው ካሳሁን መስፍን የተሰጠኝን መረጃ ተጠቅሜያለሁ፡፡

በመፈለግ ዘመዶቻቸውን ትተው ወደ ሌላ ቦታ ሄደው የሚኖሩ ሰዎች አሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ብቻቸውን የሚሆኑበት አጋጣሚ ሰፊ ነው፡፡ ስለሆነም ብቸኝነት እንዳይሰማቸውና ስነ ልቡናዊ ጉዳት እንዳይደርስባቸው በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ጉዳዮች ላይ መሳተፍ እንዲችሉ ዝምድና በመፍጠር ከማህበረሰቡ ጋር መቀላቀል አለባቸው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ዝምድና የሚፈጥሩት ከዝምድና መፍጠሪያ ስርዓቶች ውስጥ በአንዱ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን የሄዱበት ማህበረሰብ ሁልጊዜ በጥርጣሬ እንዲያያቸው ያደርጋል፡፡ ስለሆነም በነፃነት ለመንቀሳቀስ፣ እንደ ልብ ስራ ሰርቶ ለማደር እና በተለያዩ ጉዳዮች ከማህበረሰቡ እኩል ለመሳተፍ ማህበረሰቡን መቀላቀል የግድ ይሆናል፡፡ ሰው ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚሄድባቸው ምክንያቶች ብዙ ናቸው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በጥናቱ ውጤት መሰረት ስራ ለመስራት፣ በፀጥታ ችግር ምክንያት በመፈናቀል፣ የአካባቢውን ልምላሜ በመውደድ እና ለመኖርሪያነት በሚል የሚሉት ናቸው፡፡

## መደምደሚያ

የዚህ ጥናት መሰረታዊ ጭብጥ ዝምድና ከማህበረሰቡ እይታ፣ አመለካከት እና እምነት አንፃር ምን እንደሚመስል እና ዝምድና እንዲፈጠር ምክንያት (ሰበብ) የሆኑ ጉዳዮች ምን እንደሆኑ መተንተን ነው፡፡

ዝምድና በማህበረሰቡ ውስጥ መዋቅር መዘርጊያ ሰፊ ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ዘንድ ዝምድና ስጋዊና ማህበራዊ ይዘት አለው፡፡ ስጋዊ ዝምድና በመወለድ ዘርን በመቆጠር የሚገኝ የዝምድና አይነት ሲሆን ማህበራዊ ዝምድና ደግሞ ከስጋ ዝምድና ውጪ ያሉ የዝምድና ስርዓቶችን የሚመለከት ሲሆን ሰዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች ተገናኝተው ሲዋደዱ፣ ሲፋቀሩ ግንኙነታቸውን እና መዋደዳቸውን ለማፅናት እና ለማረጋገጥ የሚፈጠረውን ዝምድና የሚመለከት ነው፡፡ በጥናቱ የተጠቆሙት ማህበራዊ ዝምድናዎች ጡት መጣባት፣ ክርስትና መናሳት፣ የአደራ ልጅ ማሳደግ እና ጋብቻ ናቸው፡፡ እነዚህ ማህበራዊ የዝምድና ስርዓቶች የማህበረሰቡ አባላትን ምጣኔ ሃብታዊና ማህበራዊ ችግር በመፍታት እና ስነ ልቡናዊ ጉዳት በመጠገን ከስጋ ዝምድና ባልተናነሰ ለማህበረሰቡ ህልውና ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ ናቸው፡፡ ማህበረሰቡ ምድራዊ ህይዎቱን ምቹ ከማድረግ ባለፈ ሰማያዊ ዋጋን (ፅድቅን) ለማግኜትም ዝምድናን ይፈጥራል፡፡ ሆኖም ዝምድና በዚህ ማህበረሰብ ዘንድ ፍቅር እና ሰላም መስበኪያነት፣ መረዳጃና መጠቃቀሚያነት፣ ችግር መፍቻነት እና ማህበራዊ ግንኙነትን ማጠንከሪያነት እና ሰማያዊ ፅድቅን ማስገኛነት ይዘት አለው፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ አንድ ሰው ከቡድን ተነጥሎ ብቻውን መኖር አይችልም፡፡ ዝምድና እንዲፈጥር፣ ከሰው ጋር አብሮ እንዲኖርና እንዲቀላቀል በህይወት ውስጥ የሚያጋጥሙ አስገዳጅ ሁኔታዎች አሉበት፡፡ የተለያዩ የሃዘን እና የደስታ ማህበራዊ ጉዳዮች፣ ኑሮን ለማሸነፍ የሚሳተፍባቸው ምጣኔ ሃብታዊ ጉዳዮች እና በብቸኝነት ምክንያት የሚመጡ ስነ ልቡናዊ ስብራቶች ቡድኑ ውስጥ እንዲገባ፣ እንዲቀላቀልና እንዲዛመድ ያስገድዱታል፡፡ ዝምድና በዚህ ማህበረሰብ ዘንድ የጋራ ጥቅም (mutual benefit) ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጋር ዝምድና ሲፈጥር ሁለቱም እንዲረዳዱና እንዲጠቃቀሙ በማሰብ ነው፡፡ ሃብት ያለው በሃብቱ፣ ሃብት ንብረት የሌለው በጉልበቱ ለመረዳዳት በማሰብ ዝምድና እንደሚፈጠር ጥናቱ አመላክተዋል፡፡ ሌላው የጥናቱ ውጤት የሚያሳየው ዝምድና ሃብት ንብረት ማካፈያ (Resource sharing) መንገድ ሆኖ የሚያገለግል ስርዓት መሆኑን ነው፡፡

ዝምድና ማፅኛ፣ ማሰሪያ፣ መያዣ የሚፈልግ ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡ ሰዎች ተገናኝተው፣ ተዋደው፣ ተፋቅረው ዝምድና ሳይፈጥሩ እንዲሁ ከተለያዩ በመረሳሳት ተመልሰው የመገናኜት እድላቸው ጠባብ ይሆናል፡፡ በተለያዩ የሃዘንና የደስታ ማህበራዊ ጉዳዮች እንዲገናኙ እና ግንኙነታቸው እንዲጠናከር፣ ፍቅር እንዲዘልቅ ማሰሪያው፣ መያዣው ዝምድና መፍጠር እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ በአጠቃላይ በአዊ ማህበረሰብ ዘንድ ዝምድና በአንድ አቅጣጫ ብቻ የሚታይ ስርዓት አይደለም፡፡ ለአንድ አላማ ብቻ ተብሎ የሚፈጠር ስርዓትም አይደለም፤ እንዲፈጠር ከኋላ የሚገፉ ብዙ ጉዳዮች አሉ፡፡ የተለያዩ ፍላጎቶች፣ አስገዳጅ ሁኔታዎች፣ ተፈጥሮኣዊ ጉዳዮች፣ ጥቅሞች ወዘተ. ዝምድና እንዲፈጠር ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህ የተለያዩ ጥቅሞች እና ፍላጎቶች የሚመነጩት ከንግድና የንግድ ከባቢን አስተማማኝ ለማድረግ ካለ ፍላጎት፤ ከድህነት፣ ከእንግዳነት (አዲስነት) እና ከወገን አልበኝነት (ብቸኝነት) አንፃር እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል፡፡

## ዋቢ ፅሁፎች


መሃመድ አሊ፡፡ (2012)፡፡ *ፋይዲ ባህላዊ ጋብቻ እና የሰርግ ስነ ስርዓት በአፋር በራህሌ ወረዳ ማህበረሰብ፡፡* [ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሚያነት ጥናት]፡፡ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

ሰሚራ ኑርጌ፡፡ (2006)፡፡ *ባህላዊ የሰርግ ስርዓት በስልጤ ዞን በወራቤ ከተማ፡፡* [ያልታተመ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሚያነት ጥናት]፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

ስንታየሁ ታደሰ፡፡ (2008)፡፡ *የክርስትና አነሳስ ስርዓት ከዋኔ በሁሩታ ከተማ፡፡* [ያልታተመ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሚያነት ጥናት] ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

ሽመልስ ደገፌ፡፡ (2008)፡፡ *የአርጎባ ማህበረሰብ ባህላዊ የሰርግ ስርዓት ከዋኔ በሸዋሮቢት ከተማ፡፡* [ያልታተመ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሚያነት ጥናት]፣ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

ተችሎት ተገኘ፡፡ (2012)፡፡ *የዝምድና እሳቤ በሰሜን ሜጫ ወረዳ ማህበረሰብ፡፡* [ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ጥናት]፣ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

አለምነው አንማው፡፡ (2005)፡፡ *ባህላዊ የሰርግ ስርዓት በስናን ወረዳ በየጠድ ቀበሌ፡፡* [ያልታተመ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት ጥናት]፡፡ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

አያሌው አማረ፡፡ (2011)፡፡ የጥምቀተ ክርስትና፣ የተክሊልና የሜሮን ስርዓተ ክዋኔ ፎክሎራዊ እይታ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፡፡ [ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ጥናት]፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

አጀኢባት ወራቄ፡፡ (2011)፡፡ የውርስ ጋብቻ ስርዓተ ክዋኔ በወለኔ ማህበረሰብ፡፡ [ያልታተመ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት ጥናት]፡፡ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

አፈወርቅ ተፈራ፡፡ (2009)፡፡ *የሰርግ ስነ ስርዓት ማህበረ ባህላዊ ፋይዳ በሃራ እና አካባቢው፡፡* [ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ጥናት]፡፡ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

እመቤት ጣሴ፡፡ (2012)፡፡ *የዘመድ አዝማድ ግንኙነት ክዋኔና ማህበራዊ ፋይዳ በባህርዳር በወራሚት ቀበሌ ቀበሌ፡፡* [ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ጥናት]፡፡ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

ብሩክ ታደለ፡፡ (2013)፡፡ *በአርሲ ዞን በኅለልቻ ወረዳ በጫንሮጮ ቀበሌ የባህላዊ ስርዓተ ጋብቻ ትንተና፡፡* [ያልታተመ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት ጥናት]፡፡ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

ዝናሽ ሶሎሞን፡፡ (2004)፡፡ *የሃድያ ብሄረሰብ የባህላዊ ጋብቻ እና የሰርግ ስነ ስርዓት፡፡* [ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ጥናት]፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ደመቀ ሙጨ፡፡ (2012)፡፡ *ዝምድና አመሰራረቱ እና የከበራው ፋይዳ በፎገራ ወረዳ፡፡* [ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ጥናት]፣ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

ገነት ስመኝ፡፡ (2012)፡፡ በባህላዊ የጋብቻ ስርዓት ውስጥ የሚከወኑ ሃገረሰባዊ እምነቶች ትርጉምና ፋይዳ በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ፡፡ [ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ጥናት] ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡

የዻንዻ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ፅ/ቤት፡፡ (2015)፡፡ የዻንዻ ወረዳ አጠቃላይ ገፅታ፡፡ [ያልታተመ]፡፡

Abebayehu, T. & Dejene, G. (2019). Harmahodhaa: A traditional child fostering and fictive kinship formation among the Oromo, Ethiopia. Ethiopian Journal of social science & language studies, 6(2), 27-47. http://ojs.ju.edu.et/index.php/ejssls/index.

Alvarado, L. C. (2018). *Ritual and Fictive kinship*. University of Frieburg.

Brown, A.R.(1950). African systems of kinship and marriage (D. Forde, Ed.). Oxford University Press.

Cardoso, R. (1984). Creating kinship: the fostering of children in favela families in Brazil. In Raymond T. smith (ed.), kinship ideology and practice in Latin America (pp. 196- 203), university of north Carolina press.

Clarke, V. & Braun, V. (2015). *Thematic Analysis.* In T. Teo (Ed.), Encyclopedia of Critical Psychology, 1947-1952. Springer.

Crossman, A. (2019). Kinship: Definition in the Study of Sociology.

Creswell, J. C., & Creswell, D. (2018). *Research Design: Qualitative, quantitative and mixed mettods approach (5th ed.)* Sage publications, 257 - 258. https://lccn.loc.gov/2017044644

Durkheim, E. (1982). *The Nature of Society and Causal Explanation*. Macmillan Publishers.https://doi.org/10.1007/978-1-34916939-9_19

Gennep , A, V. (1906) Mythes et legends d'Australie. Ernest Leroux.

Getie, G. (1998). *Semantic analaysis of Amharic kinship terms in gojjam:* an anthropological approach.Insitituto italiano per 1' Africa e 1' oriente.https://www.jstor.org/stable/40761245

Gellner, E. (1958). *The concept of kinship.* University of Chicago press. http://www.journals.uchicago.edu/t-and-c

Hashim, A., Pandian, A., & Al- Shaibani, G., K (2016). An Ethnosemantic study of Affinal Kinship Terms in Arab culture. DOI: http://dx.doi.org/10.21013/jems.v3.n2.p9

James, W. (2008). Why Kinship? New Questions on an Old Topic, in early Human Kinship from Sex to Social Reproduction. Blackwell publishing. DoI:10.1002/9781444302714

Jones, R. (2011). *In 21st Century Anthropology a Refference Hand book: Kinship systems. Sage* Publications, Lee university. https://doi.org/10.4135/9781412979283.n17

Kuper, A. (2018). *We need to talk about kinship*. http://aotcpress.com/articles/talk-kinship/

Marks, J.(2002).What it means to be 98% chimpanzee: Apes, people, and their Genes. University of California press. https://doi.org/10.1525/9780520930766

Mhaiske, V.M., Patil,V. K., & Narkhede, S.S. (2016). *Forest tribology and Anthropology*. Scientific publishers.

Mumtaz, M., Ting, H., Thurasamy, R., & Cheah, J.,H. (2025). Snow ball sampling: A Review and guiedlines for survey research, *Asian Journal of Business Research*. DOI:https://10.14707/ajbr.250186

Omid, T., Golzar, J., & Noor, S. (2024). Purposive sumpling. *International journal of Education and language studies*. https://doi.org/10.22034/ijels.2025.4990681.10299

Read, D. (2018). *Kinship systems*. University of California.DOI:10.1002/9781118924396.wbiea1879

Sahlins, M. (2013). *What Kinship Is and Is Not.* The University of Chicago press.

Schneider, D. (2004). *What is Kinship all About?* In Parkin, R. & Linda Stone, L. (eds.).Kinship and family: An Ethnological Reader. Black well Publishing. http://amouroux.files.wordpress.com/2008/07/

Sousa, P. (2003). The Fall of Kinship: Towards an Epidemiological Explanation. *Journal of Cognition and Culture 3*(4), 265-303. Koninklijke Brill N.